



# እጅግ በትልቁ በኃይል እየበራ በሚንበለበል እሳት መጠመቅ

*በፓስተር ዮንግ ዱ ኪም*

[**አጠር ተደርጎ የተዘጋጀ**: ይህ ከዋናው መጽሐፍ አጠር ተደርጎ የተዘጋጀ ነው። ብዙ ክስተቶች፣ ፊት ለፊት ግጥጥሞሽ፣ ማብራሪያዎች እና ራእዮች በዚህ ጠቅለል ተደርጎ በተዘጋጀው ውስጥ አልተካተቱም። ሙሉውን መጽሐፍ እባካችሁ Amazon.com ላይ ሄዳችሁ ግዙ።]

[በትንሽ የኮሪያ ቤተ ክርስቲያን ተከታታይ የ 30 ቀናት የሌሊት ጸሎት ጊዜ፣ የቤተ ክርስቲያኗ አባላት የማይታመን መነቃቃት ገጠመኞችን አገኙ። እጆቻቸው ወደላይ ተነስተውና ሌሊቱን ሁሉ እየጸለዩ፣ ክርስቲያኖቹ መንፈሳዊ ዓይኖቻቸው ተከፈቱና ራእዮችን፣ ፈውስ፣ ኃይለኛ መንፈሳዊ ውጊያ፣ እና **ከናዝሬቱ ኢየሱስ ክርስቶስ** ጋር ፊት ለፊትም መገናኘትን አገኙ። መንፈሳዊ ዓይኖቻቸው ተከፍተው፣ በጸሎት ሰዓታቸው ጊዜ የክፉ መናፍስት ውጊያ ሲካሄድ በእርግጥ ተመልክተው ነበር። ክርስቲያኖቹ እየጸለይን እያለ እንዴት አጋንንት እኛን ለማምታታት፣ ለማስፈራራት እና ለማሳት እንደሚሞክሩ እንዲመለከቱ ተደርገዋል። በመጽሐፉ ላይ የምታገኙት እያንዳንዱ የሰይጣን መሸወጃ መንገዶች፣ እነዚህ ክርስቲያኖች መጸለይ እንዲያቆሙ አጋንንቱ ተጠቅመውበታል። ከብዙ ድራጎኖች ጋር፣ ከክፉ መናፍስት ንጉሶች ጋር፣ ከሀሰተኛ መላእክት ጋር፣ ከሀሰተኛ ክርስቶሶች ጋር፣ የሌሎችን ጭንቀት ከሚፈልጉ ክፉ መናፍስት ጋር፣ ከቫምፓየሮች ጋር፣ ቆንጆ ሴት መስለው ከሚመጡ ክፉ መናፍስት ጋር፣ ወዘተ ጋር እኚህ ክርስቲያኖች (የቤተ ክርስቲያኒቱ አባላት) ፊት ለፊት ተገጣጥመውና ተዋግተው ነበር። እነዚህ ክርስቲያኖች በተጨማሪም በኢየሱስ ብዙ ጊዜያት ወደ ገነትና ሲኦል ተወስደው ነበር። የእኩለ ሌሊት ምልጃ፣ (ከአዲስ ቋንቋ ወይም ከአዲስ ልሳን የመናገር ስጦታ ጋር አብሮ) 1 ቆሮንቶስ 12 እና 14፣ በጣም ኃይልና ጉልበት ያለው፣ አስቸጋሪና ፍሬያማ የጸሎት ሰዓት እንደሆነ ተገልጿል። ተከታታይ 5 መጽሐፍት አሉ፣ ይሄኛው የመጀመሪያው መጽሐፍ ብቻ ነው። የዋናው መጽሐፍ አካል ያልሆኑ ስዕላት ተጨምረዋል።]

ማስታወሻ:- የመጽሐፉ ርዕስ በእንግሊዝኛው "Baptize by Blazing Fire" የሚል ነው።

***ከኢየሱስ ለፓስተር ኪም:***

***"ከአሁን ጀምሮ ወደፊት፣ አንተና የቤተ ክርስቲያኗ አባላት የምታዩትን ገጠመኞች፣ የምታዩትንና የምትሰሙትን አብራርተህ በመጻፍ ማስቀመጥ አለብህ። በዚህ፣ በኮሪያና በዓለም ዙሪያ ያሉ አብያተ ክርስቲያናት እንዲነቁ እሻለሁ። ወደዚህ ምድር የመጣህበት ምክንያት ይህ ነበረ . . . በዚህ ሰዓት የኮሪያ አብያተ ክርስቲያናት የውስጥና የውጪ ታማኝ መተዳደሪያ እኔ ለእነሱ ካሰብኩላቸው ጋር በመጋጨት ላይ ይገኛል፤ መንፈሳዊ መሪዎችና የቤተ ክርስቲያን አባላት እኔን ኢያመለኩኝ ያለው በደንብ(በልምድ) እና እኔን በተጻፈ ንድፈ ሀሳብ(አስተያየት) ብቻ ነው የሚያውቁኝ።"***

**ፓስተር ኪም:**

የቤተ ክርስቲያናችን አባላት በአዲስ ቋንቋ (በልሳን) የመናገር ኃይል ያምናሉ፣ ስለዚህ ረዘም ላለ ጊዜ፣ ብዙ ትኩረት ሰጥተን እና በጣም በጥልቀት መጸለይ ችለን ነበር። በተጨማሪ በአዲስ ቋንቋ መጸለያችን እንድናተኩር ረድቶናል፣ እናም በዛ መንፈሳዊ ዐይናችንን የከፈተ ለማመን የሚያስቸግር ብቃት መጣ። የአንድን ግለሰብ መንፈሳዊ ዓይኖች የማስከፈት ሂደት አስቸጋሪ ብቻ አልነበረም፣ ግን አንድ ሰው ብዙ መሠናክሎችን የግድ ማለፍ ነበረበት። በመሆኑም በግዴለሽነት የምትረሱ (ትኩረት የማትሰጡ) እና በሚያስፈልገው ሁሉ የማትዘጋጁ ከሆነ፣ በትልቁ ብዙ ዋጋ ትከፍላላችሁ። አሁን እኛም ጭምር፣ በጥንቃቄ ከምስጋና ጋር፣ በ**ኢየሱስ** ቃላት ልባችንን እየሞላን፣ በትኩረትና በግልጽ ወደ **ጌታ** እያለቀስን ራሳችንን እያዘጋጀን መልሰን ለማጥቃት በታላቁ ተዘጋጅተናል።

የሰይጣን መልእክተኞች ለየብቻቸው ይመጣሉ። ከዛ አንደኛው ሲሸነፍ፣ ሌሎች ሁለት ተጨማሪ ይቀርባሉ፤ ከዛም እነሱ ለአስር፣ ለሰላሳ፣ ለአምሳ፣ ለአንድ መቶ፣ እና ከዛም በላይ በሆኑ ቁጥሮች ተደራጅተው ያጠቃሉ። የተደራጁት በፍጥነት ይበተኑና ከዛም እንደ ሁኔታው አይነት በድጋሚ ይሰባሰባሉ።

ከዛ አንዱ በአንድ ጸሎት ሲባረር፣ ክፉ መናፍስቱ ወደ ቀጣዩ ትኩረታቸው በቁጣ፣ በጣታቸውና በሹል ነገር እየጠቆሙ፣ እየፈተኑ፣ እና አንዳንዴም በሚያምር ወሬ እያንሾካሾኩ ይንቀሳቀሳሉ። በመጨረሻም፣ ማንነታቸው ሲጋለጥ፣ እነሱ በፍጥነት ሮጠው ይሄዳሉ። የሰይጣን መልእክተኞች በተለያዩ መልኮች ከፊታችን ይገለጣሉ።

አንዳንዴ ታዋቂ አጫዋቾች፣ ንፁህ ህፃን ልጅ፣ ሀሰተኛ ኢየሱስ፣ ወይም እንደ ቆንጆ የብርሃን መልአክ በመምሰል እኛን ሊያጠምዱን ይፈልጋሉ (2ኛ ቆሮንቶስ 11:14)። ነቀፋ ያለባት አስመስለው ሴት ልጄን መስለው ሲገለጡ ወደ ግራ መጋባት ጭምር እኛን ከተውናል። እኛ ከክፉት መናፍስቶች ጋር ብዙ ውጊያዎችን (ጦርነቶችን) ተዋግተን አሸንፈናል፣ ግን ተሸንፈንም እናውቃለን። በሽንፈታችን አእምሮን የሚያሳምም ቁጭቶች በስጋችን መጥቶብናል። ህመሙ በጣም ኃይለኛ በመሆኑ እኛ ብዙ ጊዜ መሬት ላይ በመንከባለል እና በድንገትም እንወድቅ ነበር። እኛ ሊታሰቡ ከማይቻሉ አስፈሪ የክፉት መናፍስት ጋር ፊት ለፊት በተጋጠምን ጊዜ፣ **ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ** ሊቀ መላእክት ሚካኤልንና ሰማያውያን መላእክትን እንዲያግዙን ያዘጋጅልን ነበር። ጦርነቱን(ውጊያውን) ተከትሎ በድካም ብዛት ስንወድቅ ሰማያውያን መላእክት እንዲያግዙን ስንጠራ ብቻችንን እንዳልሆንን አፍቃሪ **ጌታችን** አረጋግጦልናል።

**ኢየሱስ** ራሳችንን በየቀኑ በጸሎት እንድናዘጋጅ አስታውሶናል (ማርቆስ 9:29)። ቀጣይነት ያለው ጸሎት መኖር(መጸለይ) አስፈላጊ ነው። ሁለት ወይም ከዛ በላይ ምስክር በመሆን የመጸለይን ጥቅም **ኢየሱስ** አብራርቷል (ማቴዎስ 18:19)። የክፉት መናፍስት(አጋንንቶች) በእርጋታ ለቀው አይሄዱም። ከዛ በተለየ፣ እነሱ ሰንበሮችን ይተዋሉ፣ እናም ሥቃዩ ይቀጥላል።

የእኛ የ2005 አጭር መልእክት "**በጸሎት የተነቃቃችሁ ሁኑ**፣" የሚል ነበር እናም የአንድነት ጸሎታችንን በ ጃንዋሪ 2 ጀመርን። ለሰላሳ ቀናት የቀጠለ ነበር። በአጠቃላዩ አስር አባላት ነበሩ። በመጀመሪያው ቀን፣ ከእሁድ ምሽት አገልግሎት በኋላ፣ እኛ የጸሎት አገልግሎት ነበረን። በሁለተኛው ቀን (ጃንዋሪ 3)፣ **የመንፈስ ቅዱስን** በእሳት መገኘት እውቀት (ብቃት) አገኘን። የሕብረት ጸሎቶች እንዲሁም የግል ጸሎቶች መቆጣጠር በማይቻል መልኩ ተጠናክረው እና እስከ ጠዋቱ 1:30 ቀጣዩ ቀን ድረስ ቀጥለዋል። የጸሎት አገልግሎት ካለቀ በኋላ፣ እኛ ክብ ሰርተን በመሰባሰብ ምስክርነቶችን እና በትክክል ኢየሱስን ማግኘት ምን እንደሚመስል እንሰማለን። የጸሎት አገልግሎቶቻችን ሰዓት እየረዘመና እየረዘመ መጣ። ረቡእ የምሽት አገልግሎት ማታ 1:30 ጀመረ፣ ግን በነጋታው ጠዋት 2 ሰዓት ላይ ተገባደደ። ሐሙስ ከምሽቱ 3 ሰዓት እስከ ጠዋቱ 4 ሰዓት።

**እግዚአብሔር** አስተሳሰባችንን በጠቅላላው ገለበጠው(ቀየረው)። ብዙ በጸለይን ቁጥር፣ **ጌታም** በሚያስደንቁ ነገሮች በብዛት ጫና ያደርግብን ነበር። ምንም እንኳ አገልግሎታችን ሌሊቱን ሙሉ ቢቆይም፣ ማንም ቅሬታ አያቀርብም ነበር። ቅሬታ ከማቅረብ በተቃራኒ፣ ብዙ መንፈሳዊ ምግብን ይሹ ነበር። እየጸለይን ባለንበት ጊዜ **ጌታ** ሊጎበኘን መጥቶ ነበር። እኛ እርሱን በመንፈሳዊ ዓይኖቻችን አይተነዋል፣ ነገር ግን አንዳንድ ጊዜ እኛ እርሱን በስጋዊ ዓይናችን በግልጽ እናየው ነበር።

ልጆቹ **ኢየሱስን** ሲያገኙት፣ እነሱ ካለመታዘዝ የተነሳ ይፈሩና ወደ የዋህ ታዛዥነትና ታማኝ አገልጋይነት ይለወጣሉ። ሁለቱ አባላቶቻችን፣ ገነትና ሲኦልን ካዩ በኋላ፣ በጉልበታቸው ተንበርክከው አለቀሱና፣ እኔ ላይ ያልተገቡ ሁኔታዎችን ላደረጉባቸው ጊዜያት ይቅርታ ጠየቁኝ። የአየር ሁኔታው ከዜሮ በታች በሆነባቸው ቀናት የእጆቻቸው መዳፍ ላይ ሞቃት ትንፋሽ እያደረጉ ወንጌልን ለሌሎች ለማካፈል ወደ ውጭ ይወጡ ነበር። እነሱ ከሰዓት 10 ሰዓት ላይ ወደ ውጭ ይወጡና እጆቻቸውና እግሮቻቸው ቀዝቅዘውም፣ ከምሽቱ 2:30 እስኪሆን ድረስ አይመለሱም። ታማኝ ብርቱ አገልጋይ መሆን እንዳለባቸው እነሱ አውቀው ነበር ምክንያቱም ሀብታቸው በሰማይ(በገነት) ሲከማች አይተዋልና። ሚና(Meena)፣ የ5 ዓመቷ ልጅ፣ ክንዶቿ ወደ ላይ ተነስተው ከ2 እስከ 3 ሰዓታት! ያህል በልሳን ትጸልያለች። የቤተ ክርስቲያናችን አባላት ቅዱስ ስጦታዎችን ትንቢት የመናገር፣ መናፍስትን የመለየት፣ በልሳን መናገር፣ እውቀት፣ ጥበብና ቅዱስ እምነት ተቀብለዋል።

በዚህ መጽሐፍ ውስጥ ምንም ውሸት የሆኑ ይዘቶች የሉም። በጸሎት ጊዜያት የአባላት የግል ገጠመኞች ብቻ ተካተዋል።

የጌታ ቤተ ክርስቲያን አባል (The member of Lord's Church) : [ፓስተር ኪም Pastor Kim] [ካንግ, ህዩን-ጃ Kang, Hyun-ja] [ኪም, ዮሴፍ Kim, Joseph] [ኪም, ጁ-ኢዩን Kim, Joo-Eun] [እህት ቤይክ, ቦንግ-ንዮ Sister Baek, Bong-Nyo] [ሊ, ሀክ-ሱንግ Lee, Haak-Sung] [ሊ, ዩ-ክዩንግ Lee, Yoo-Kyung] [ሚና Meena] [ኦህ, ጆንግ-ሱክ Oh, Jong-Suk] [ዲያቆኒት ሺን, ሱንግ-ክዩንግ Deaconess Shin, Sung-Kyung] [ኦህ, ጁንግ-ሚን Oh, Jung-Min]

## ==== ቀን 1 ====

## ==== ቀን 2 ====

**ፓስተር ኪም:**

በ**መንፈስ ቅዱስ** ልዩ እገዛ (እርዳታ)፣ እየጸለይን ባለበት ጊዜ እሳት ላይ እንዳለን ነበር ሁኔታው። ምንም እንኳ አገልግሎታችን በቀጣዩ ቀን ከጠዋቱ 1 ሰዓት በኋላ ቢጠናቀቅም፣ እኛ በቂ እንደሌለን (በቂ አገልግሎት እንዳላደረግን) ተሰማን።

**ሊ, ዩ-ክዩንግ:**

እኔ እጅግ በጣም በጥልቀት ፈልጌውና በሁሉም ኃይሌ ወደ ጌታ ተጣራሁ፣ *"**ኢየሱስ**፣ **ኢየሱስ** እወድሃለሁ(አፈቅርሃለሁ)። አንተን እንዳይህ አድርገኝ። ለኔ ተገለጥልኝ።"* ጮህኩና በትጋት በልሳኖች ጸለይኩ። ወደ አንድ ሰዓት ካለፈ በኋላ፣ በድንገት አንድ ታላቅ ብርሃን በራ፣ እና አንድ ሰው ብርሃኑ ውስጥ ቆሞ ነበር። ዐይኖቼን ከፈትኩና በታላቅ አግራሞትና ድንጋጤ ተሞላሁ፣ ግን ምንም ነገር አላየሁም። ዐይኖቼን በድጋሜ ስዘጋ፣ በግልጽ ማየት ችዬ ነበር፣ ስለዚህ ዐይኖቼን ዝግ ሆነው አቆየኋቸው። **ኢየሱስ** የሚያበራና የሚያንጸባርቅ ልብስ ለብሶ ከፊቴ ቆሞ ነበር። ***"ዩ-ክዩንግ፣ አፈቅርሻለሁ(እወድሻለሁ)"*** **ኢየሱስ** እነዚህን ቃላት ተናገራቸው፣ ከዛ በይበልጥ ወደእኔ ቀረበና ከፊቴ ተቀመጠ። እንደ እርሱ የሚያምር ሰው በፍፁም ያየሁ አይመስለኝም። የ**ኢየሱስ** ጸጉር ወርቃማና የሚያማምሩ ትልልቅ ዐይኖች አሉት። **ኢየሱስ** ረጋ ባለ መልኩ ጸጉሮቼን ዳሰሳቸውና እንዲህ አለ:- ***"ዩ-ክዩንግ፣ አፈቅርሻለሁ"*** ማልቀስ ጀመርኩ እና ልቤም ቀለጠ። ***"ገነት ምን እንደሚመስል ላሳይሽ እፈልጋለሁ፣"*** ከትንሽ ቆይታ በኋላ መንገዱ ላይ ነበርን፣ በጣም የሚያበራና የሚያንጸባርቅ ብርሃን ነበረ ስለዛም ዓይኖቼን መግለጥ አልቻልኩም። *"ይህ ገነት መሆን አለበት"* ብዬ አሰብኩኝ። እንደደረስን፣ ሊቆጠሩ የማይችሉ፣ ክንፎች ያሏቸው መላእክት ተቀበሉን፣ እናም **ኢየሱስ** ከብዙ መላእክት ጋር እያስተዋወቀኝ የተለያዩ ቦታዎች ወሰደኝ። በኋላም **ኢየሱስ** ይህን ጠየቀኝ:- ***"ዩ-ክዩንግ፣ ገነትን እየጎበኘሽ ስለሆነ ደስተኛ ነሽ?"*** *"አዎ፣ **ኢየሱስ**፣ በጣም፣ በጣም ደስተኛ።"* **ኢየሱስ** እንዲህ አለ፣ ***"በትጋት ጸልዩ፣ ፓስተር ኪምን ታዘዢው፣ እና በቤተ ክርስቲያን አገልግሎቶች በመልካም ተገኚ(ተካፈዪ)፣ ከዛም በጣም በተደጋጋሚ ገነትን እንድትጎበኚ እኔ እወስድሻለሁ፣ ስለዚህ ቀናኢ ሁኚ።"***

አገልግሎቱ ከተጠናቀቀ በኋላ **ኢየሱስ**ን ማግኘቴንና ገነትን መጎብኘቴን አካፈልኩ።

**ቤይክ, ቦንግ-ንዮ:**

እያንዳንዳችን ለመጸለይ የመሬት ወንበሮች ላይ ከታች ተንበርክከን ነበር። ከእኔ ቀጥላ የፓስተሩ ሚስት ነበረች፣ በ**መንፈስ ቅዱስ** ተሞልታ እየደነሰች(እያሸበሸበች) የነበረችው። የእርሷ ዳንስ ለስለስ ያለ ነበር፣ ልክ እንደሚፈስ ውሀ። እርሷ ብሩህ ሆና እና መንፈስ ቅዱስ እንደመራት በሚያምር መልኩ እየደነሰች ነበር።

እኔ በልሳኖች መጸለይ ቀጠልኩ። ድንገት አንድ ታላቅ ወርቃማ ብርሃን በራ፣ እናም እዛ የሚያበራ ነጭ ልብስ ለብሶ **ኢየሱስ** ቆሞ ነበር። ***"ቦንግ-ንዮ። አፈቅርሻለሁ።"*** **ኢየሱስ**ን የማግኘት ታላቁን የደስታ ፍሰት ቃላቶች ሊገልጹት አይችሉም። ለእርሱ ብዙ ጥያቄዎች ነበሩኝ፣ እና እርሱም ወዲያውኑ ይመልሳቸው ነበር።

**ሊ, ሀክ-ሱንግ:**

እኔ በልሳኖች መጸለይ ላይ አተኩሬ ነበር፣ ያለኔ እውቀት፣ ድምጼ ኃይለኛ ስለነበረ ጸሎቴ በሥልጣን ተሞልቶ ነበር። አካሌ ልክ እንደ እሳት እየነደደ ነበር፣ እናም የውጨኛውን ልብሶቼን ማውለቅ ነበረብኝ። ከቆይታ በኋላ፣ ሸሚዜ በላብ ርሶ ነበር።

የ**መንፈስ ቅዱስ** ኃይለኛው የነበልባል እሳት በእኔ ላይ እንዲህ ሲመጣ በሕይወቴ በፍፁም አጋጥሞኝ አያውቅም። ለመጸለይ ደስተኛ እና ደስተኛ ነበርኩ። በጉልበቴ ተንበርክኬና ተጎንብሼ ጸለይኩኝ፣ እናም በሚያሳምም የሰውነት መስለል፣ እግሮቼ ደነዘዙ።

**የፓስተሩ ሚስት፣ ካንግ, ህዩን-ጃ:**

ተገቢ(መልካም) የሆነ ጸሎት ለረጅም ጊዜያት አልጸለይኩም ነበር፣ ስለዚህ የአስቸኳይነት ስሜት ተሰማኝ። እየጸለይን እያለ፣ ያልተለመደ መንፈሳዊ ሁነታ(environment) ከተነሳ፣ **ጌታ** ከፓስተሩና ለየብቻ ከእያንዳንዱ አባላት ጋር በቁጡ (በኃለ) ስልጣን ይዋዋላል። ወይዘሮ ቼ ቶማስን **ጌታ** ቀብቷት የነበረው መንፈሳዊውን ዳንስ፣ ለመቀበል እጓጓ ነበር። እናም በኋላ፣ ለመጀመሪያ ጊዜ ያለማመንታት ለመደነስ ቻልኩ። ለተወሰነ ጊዜ ይህንን ስጦታ ደብቄው ነበር። ነገር ግን ከ**መንፈስ ቅዱስ** የመሪነት ኃይሎች ሮጨ መሄድ አልቻልኩም። አካሌ በእሳት ተቀብቶ እጆቼም በነጻነት ከሙዚቃው ጋር ይንቀሳቀሱ ነበር።

# ==== ቀን 3 ====

# ==== ቀን 4 ====

**ሊ, ዩ-ክዩንግ:**

በሁሉም ኃይሌ እየጸለይኩ ነበር እና በአንደ ድንገተኛ የኃይል ፍንዳታ፣ ከአንድ ፊልም የወጣ የሚመስል አንድ ሰይጣን አየሁ። ነጭ ልብስ ለብሶ እና ረጅም ጸጉር ነበረው፣ እየደነሰና ቀፋፊ በሆነ ድምጽ:- *"ሃ ሃ ሃ ሃ ሃ ሄ ሄ ሄ ሄ ሄ"* እያለ ወደ እኔ መጣ። በፍርሃት ሽባ ሆኜ ነበር። *"አንተ ክፉና የተረገምክ ሰይጣን። ከእኔ እንድትሸሽ **በኢየሱስ ስም** አዝሀለሁ።"* ነገር ግን ሰይጣኑ እንዲህ እያለቀሰ ወደኔ ቀረበ:- *"ሄ ሄ ሄ ሄ፣ ለምንድን ነው እኔ የምሸሸው?፣ አንቺን ከጸሎት ለማደናቀፍ እኔ ብቻ አይደለሁም እዚህ ያለሁት፣ ነገር ግን አካላዊ ህመም እሰጥሻለሁ።"* ከዛ ፓስተር ኪም እጁን ራሴ ላይ አደረገና እየጮኸ ጸለየ፣ *"አንተ የቆሸሸክ ሰይጣን። **በኢየሱስ ክርስቶስ ስም** እንድትሸሽ አዝሃለሁ።"* ሰይጣኑ ሄዶ ነበር። ፓስተሩ ይህን ነግሮን ነበር፣ *"ስንጸልይ የግድ ልበ ሙሉ (confident) መሆን አለብን።"*

***"ኢየሱስ፣ እርዳኝ። እርዳኝ።"*** ብዬ እየተጣራሁ መጸለይ ቀጠልኩ። ለተወሰኑ ጊዜያት ወደ እርሱ እየተጣራሁ ነበር፣ በደማቅ ብርሃን ውስጥ ኢየሱስ ተገለጠ። እርሱም ለእኔ እንዲህ ተናገረ:- ***"ዮንግ-ክዩንግ፣ አትጨነቂ። እኔ እጠብቅሻለሁ. . . ማንኛውም አይነት ሰይጣኖች ቢያጠቁሽም እንኳ፣ አትፍሪ አትጨነቂም። በሁሉም ጥንካሬሽ ወደ እኔ ተጣሪ እናም እኔ እመጣና ሰይጣኖቹን ወደዛ አወጣቸዋለሁ። ስለዚህ፣ አትፍሪ እና ጠንካራ ሁኚ።"***

# ==== ቀን 5 ====

**የጸሐፊው ማስታወሻ:** የእህት ቤይክ, ቦንግ-ንዮ እና የ**ኢየሱስ** ጋብቻ፣ በአዳኙና እርሱ ባዳናቸው ኃጢአተኞች መካከል ያለውን ግንኙነት ያመለክታል። ይህንን ለአዲሷ አማኝ ለቤይክ ማሳየት ፈልጎ ነው።

**ቤይክ, ቦንግ-ንዮ:**

ከአገልግሎት በኋላ በትጋት በልሳኖች መጸለይ ጀመርኩ፣ **ጌታ**ም ተገለጠልኝና እንዲህ አለ፣ ***"ቦንግ-ንዮ፣ ወደ ገነት እንሂድ።"*** እርሱ እጄን ያዘና መራኝ። ከቆይታ በኋላ፣ **ከሰማያዊው አባታችን ቅዱስ** ዙፋን በታች ቆሜ ነበር። ኢየሱስ ወደ ገነት የመጣሁበትን ምክንያት ፍቅር በተሞላበት ሁኔታ አብራራ: ***"ቦንግ-ንዮ፣ ዛሬ ከአንቺ ጋር የሚያምር የሰርግ ስነ ስርዓት በገነት ማድረግ እመኛለሁ፣ እናም ለዛ ነው እኛ እዚህ ያለነው።"***። ከቆይታ በኋላ መላእክት ልብሴን ማዘጋጀት ጀመሩ እና በብዙ የከበሩ የድንጋይ ፈርጦች አስጌጡኝ። ለእኔ እንደተዘጋጀው የወርቅ ልብስ አይነት በፍፁም አይቼ አላውቅም። በደስታ ተሞልቼ ነበር። ብዙ መላእክትና የገነት ዜጎች ስለኛ ጋብቻ የደስታ መግለጫ አቀረቡ፣ እናም እኔ ይህንን ሁኔታ በፍጹም አልረሳውም። ከዛ ቀጥሎ **የሰማያዊው አባታችን** ቅዱስ ዙፋን በጣም በቀስታ ወደኋላና ወደፊት የሚንዠዋዠው ይመስል ነበር። በእያንዳንዱ ጊዜ የእርሱ ቅዱስ ዙፋን ሲንቀሳቀስ፣ ምክንያቱም **እግዚአብሔር** በጣም ስለተደሰተ፣ በጣም የሚያበሩ ደማቅ ቀለሞች ፈንጥቀው ይወጡ ነበር። ከስነ ሥርዓቱ በኋላ፣ የ**ጌታ**ን እጅ ይዤ በገነት ሁሉ ተጓዝኩ። እኔ በደስታዬ ጫፍ ላይ:ነበርኩ።

**ሊ, ሀክ-ሱንግ:**

በጽኑ ቆራጥነት፣ በልሳኖች መጸለይ ጀመርኩ፣ በድንገት፣ መስቀል ደማቅ ብርሃን እየፈነጠቀ ከመድረኩ ጀርባ ተንጠልጥሎ፣ እና አንድ ክብ በር ታየ። ከትንሽ ቆይታ በኋላ፣ **ኢየሱስ** ብቅ አለ። ***"ሀክ-ሱንግ። አፈቅርሃለሁ።"*** በእኔ ላይ የበዛውን ደስታ ልሸከም አልቻልኩም። ***"ሀክ-ሱንግ፣ ከእኔ ጋር መሄድ ያለብህ አንድ ቦታ አለ፣ ስለዚህ እንሂድ።"*** **ኢየሱስ** እጄን እንደያዘ፣ አካሌ ልክ እንደላባ በቀለለ መልኩ አየር ላይ ተንሳፈፈ። መዳረሻችን ላይ እንደደረስን፣ እንግዳ የሆነ አንድ ክርፋት ነበር፣ እና በጣም ቆሻሻ ነበር። በዙሪያዬ ከነበረው መጥፎ ሽታ የተነሳ፣ በችግር ነበር የምተነፍሰው። *"**ኢየሱስ**፣ የኔ ወዳጅ **ኢየሱስ**። የት ነው ያለነው? ከፊቴ በደንብ ማየት አልቻልኩም፣"* ጮህኩኝ፣ **ኢየሱስ** ግን እንዲህ አለ:- ***"ሀክ-ሱንግ፣ አትፍራ። ይሄ ሲኦል ነው። እኔ እጠብቅሃለሁ፣ ስለዚህ አትጨነቅ። ግን በቅርበት ተመልከት።"***

እሳቱ የሲኦልን መግቢያዎች ደማቅ ቀይ አድርጎ አግሏቸዋል፣ ከመግባታችን በፊት እንኳ ሊቋቋሙት የማይችሉት ሙቀት ነበር። ከሚያንገበግበው ሞቃት እሳትና ከኃይለኛው ሙቀት መራቅ ነበረብኝ። እኔም ጠየኩኝ፣ *"**ኢየሱስ**፣ እንዴት ነው ወደዚህ የእሳት ጉድጓድ ውስጥ ተራምደን የምንሄደው? ይህን ማድረግ የምችል አይመስለኝም።"* ጥቅጥቅ ወዳለው የጨለማ ቦታ ሄድን እናም አንድም ነገር ማየት አልቻልኩም። ከዛ፣ ኢየሱስ አይኖቼን እንደነካ፣ ከዛ በግልጽ ማየት ቻልኩ። አንድ አሮጊት ሴትዮ ተስፋ በማጣት ውስጥ ሆና ያለ እንቅስቃሴ ቁጭ ብላ እና የኮሪያን ነጭ ባህላዊ ልብስ ለብሳ ነበር። **ኢየሱስ** አዘዘ፣ ***"ሀክ-ሱንግ፣ በቅርበት ተመልከት፣"*** ስለዚህ ወደ አሮጊቷ ሴት በቅርበት ተራመድኩ። እርሷ ከጥቂት አመታት በፊት ያለፈችው ቅደመ አያቴ ነበረች። እናቴ ቤት ትታ ስትሄድ፣ ቅድመ አያቴ አሳደገችኝ። ቅድመ አያቴ ትወደናለች። ቅድመ አያቴ በሲኦል በመሆኗ ትክክል አልነበርኩም። ተደንቄ ወደ እርሷ ጮህኩኝ፣ *"ቅድመ አያቴ፣ እኔ ነኝ፣ ሀክ-ሱንግ። እንዴት ነው ረጋ ያለና ቅን ሰው ፍጻሜው እዚህ ሊሆን የቻለው? ፍጠኚ፣ ከዛ ውጪ።"* ቅድመ አያቴ በፍጥነት አወቀችኝ፣ እና ተገረመች፣ እሷም ጠየቀች፣ *"ሀክ-ሱንግ፣ ለምንድን ነው እዚህ ያለኸው? እንዴት እዚህ መጣህ?"* እኔም መለስኩ፣ *"**ኢየሱስ** እዚህ አመጣኝ። ቅድመ አያቴ፣ ፍጠኚና ከዛ ውጪ።"* ቅድመ አያቴ አለቀሰችና ጮኸች፣ *"ሀክ-ሱንግ፣ መውጣት የምፈልገውን ያህል፣ እዚህ የምትፈልገውን አታደርግም። በፍጻሜህ እዚህ መሆን የለብህም። አሁኑኑ ለቀህ ውጣ።"* በእንባ እኔ ኢየሱስን ተማጸንኩት፣ *"**ኢየሱስ**፣ እባክህን ቅድመ አያቴ እንድትወጣ እርዳት። ቅድመ አያቴ አሳዛኝ ሕይወት ኖራለች።"* ከመቅጽበት፣ አንድ ትልቅ እባብ ከቅድመ አያቴ እግር በታች ብቅ አለ እናም ይጠመጠምባትና አካሏን ይጠመዝዘው ጀመር። እኔም በኃይል ጮህኩኝ፣ *"አህህ።"* ቅድመ አያቴ በፍርሃት ጮኸች፣ *"አድነኝ፣ እባክህን፣"* ግን ምንም ጥቅም የለም። *"**ኢየሱስ**፣ የእኔ ተወዳጅ **ኢየሱስ**፣ እኔ ነኝ ብዙ ክፉ ነገሮችን ያደረኩ፣"* አለቀስኩኝ፣ *"እባክህን አንድ ነገር አድርግ፣ እባክህን።"* **ኢየሱስ** አንድም ቃል አልተናገረም። ነገር ግን ሲመለከት ልቡ ተሰብሮ ነበር። ስለምን እያለቀስኩ እና እያለቀስኩ ነበር፣ ግን ምንም ጥቅም የለም። በእብድነት መሀል ሆና እንኳ፣ እሷ ስለ ቤተሰቡ ደህንነት ትጠይቅና ስለነሱ ትጨነቅ ነበር። *"ሀክ-ሱንግ፣ እህቶችህ እንዴት ናቸው? እናትህስ?"* እኔም እንዲህ ብዬ መለስኩ፣ *"ሁሉም መልካም ነው(ጥሩ እያደረገ ነው)።"* እና እየመለስኩላት እያለ፣ እባቡ ወገቧ ላይ ተጠመጠመ። የቅድመ አያቴ የሥቃይ ጩኸቶች እያየሉ እያየሉ መጡ። **ኢየሱስ** እጄን ያዘና እንዲህ እያለ መራኝ:- ***"ሀክ-ሱንግ፣ አሁን የመሄጃ ሰዓት ነው።"*** የቅድመ አያቴን ለቅሶዎች ከበስተ ኋላዬ ትቼ ከሲኦል ወጣሁኝ። **ኢየሱስ** እንዲህ አለ:- ***"በሲኦል፣ ከግዙፉ ዓለም ጋር ሲወዳደር፣ ሁሉም የስሜት ህዋሳትህ በበለጠ መልኩ በእርግጠኝነትና በግልጽ ይኖራሉ. . .ሀ-ሱንግ፣ አታልቅስ። አንተ በግልጽ አይተኸዋል፣ ስለዚህ ሂድና ጌታን በታማኝነት አገልግለው። ተረዳህ?"***



ከቆይታ በኋላ **ኢየሱስ** ጠራኝና:- ***"ሀክ-ሱንግ፣ ሲኦል አሰቃቂ ነበር፣ ትክክል? ዛሬ ገነትን ላሳይህ እፈልጋለሁ።"*** በአጭር ጊዜ ውስጥ፣ በገነት ውስጥ ነበርን። የመላእክት ማህበራት እና ከእኔ በፊት ገነት የደረሱ ብዙ ሰዎች ሊቀበሉን መጡ። በዙሪያው የነበሩ መላእክት እና **ኢየሱስ** በአንድነት በደስታ ለመደነስ እጅ ለእጅ ተያያዙ። ሁሉም ነገር ስለ ገነት በሲኦል ከነበሩት ሁኔታዎች ሙሉ ልዩነት ነበረው። በገነት፣ ያየሁት ታሪክ፣ አስገራሚ፣ የማይታመን ይመስላል። በገነት እያለሁ፣ ለ**ኢየሱስ** አንድ ጥያቄ አቀረብኩ፣ *"**ኢየሱስ**፣ የፓስተሩ ልጅ፣ ዮሴፍ-- እግሮቹ በሚያሳምም ኪንታሮት ተሸፍኗል እናም በችግር ነው መራመድ የሚችለውም። እባክህን ፈውሰው። እና እናቴ በጀርባ ህመም እየተሠቃየች ነው። በህመም እንዳትሆን እርዳት። በቤተ ክርስቲያን ቢሮ ውስጥ እየኖረ ያለውን ወንድም አህ, ጆንግ-ሱክን በፍጥነት ስራ እንዲያገኝ እርዳው። እናም በመጨረሻ፣ በቤተ ክርስቲያናችን መነቃቃት እንዲኖር እርዳን።"* **ኢየሱስ** በደስታ መለሰ፣ ***"አዎ፣ መልካም።"*** **ኢየሱስ** ወደ እኔ ተመለከተና እንዲህ አለ፣ ***"ሀክ-ሱንግ፣ ለዛሬ ያ በቂ ነው። እንሂድ።"*** **ኢየሱስ** እጄን ሲይዘኝ፣ በሰማይ ውስጥ በረርን፣ ተመልሰንም ቤተ ክርስቲያን ደረስን።

በትጋት መጸለዬን ቀጠልኩ። በሲኦል እየተሠቃየች ስላለችው ቅድመ አያቴ ማሰብ ማቆም አልቻልኩም፣ እናም በእንባ ተሞላሁ። በታላቅ ሀዘንና ህመም ላይ ነበርኩ፣ እየተወራጨሁና እየጮህኩኝ አለቀስኩኝ፣ *"ጌታ ሆይ፣ ምንድነው የማያደርገው? ቅድመ አያቴ በእኔ ምክንያት ነው የሞተችው። ይህ ልቤን በጣም ያሳምመዋል። ቅድመ አያቴ። ድሃዋ ቅድመ አያቴ።"* ሙሉ ለሙሉ እስኪደክመኝ ድረስ አለቀስኩኝ። ከዛ በድጋሜ ጀመርኩ። ወደ ጌታ ተጣራሁ። አልፎ አልፎ አለቅሳለሁ። ለ2፣ ለ3፣ እና ከዛም ለ4 ሰዓታት የፈሰሱትን እንባዎች ላምን አልቻልኩም። የመጀመሪያው የጸሎት ክፍለ ጊዜ ተጠናቀቀ፣ ግን እስካሁን ሀዘኔን ልሸከመው አልቻልኩም። ገነትና ሲኦልን የመጎብኘቴን ምስክርነት ከሌሎች ጋር አካፈልኩ። ከዛ ጠዋት 11 ሰዓት ላይ ሁለተኛውን የጸሎት አገልግሎታችንን ጀመርን፣ አገልግሎቱም ከ5 ሰዓታት በኋላ ተጠናቀቀ። ፓስተር ስብከቱን እየሰጠ እያለ፣ **ኢየሱስ** ተገለጠ፣ እናም ከዛ የፓስተሩ ስብከት የበለጠ ኃይለኛ እየሆነ መጣ። መላእክት ከሰማይ ወደ ታች መጡ፣ ስብከቱ ከሚተላለፍበት አጠገብ ሰልፍ ሰርተው ነበር፣ አንዳንዶቹ ከመያዣ ጋር ክብ ጎርጓዳ ሣህን ይዘው ነበር። እነሱ እያንዳንዱን ጸሎታችንን ይይዙ ነበር። እናም እነሱ፣ *"አሜን። አሜን።"* እያሉ ዘመሩ።

ሁሉም አገልግሎቶች ከተጠናቀቁ በኋላ እንኳ፣ በሲኦል ስላለችው ቅድመ አያቴ በታላቁ እየተጨነኩ መቆጨቴን ማቆም አልቻልኩም።

# ==== ቀን 6 ====

<u>**ቤይኪ, ቦንግ-ንዮ:**</u>

ፓስተር ስብከቱን ከጀመረ 4 ሰዓታት አለፉ። አንዳችንም እንኳ ለአፍታ ዓይኖቻችንን አልከደንም። በተጨማሪ የ አምስት ዓመቷ ልጅ ሚና ስብከቱን በትኩረት እያዳመጠች ነበር። አይኖቼን ፓስተሩ ላይ አተኩሬ ሳለ፣ **ኢየሱስ** ከብዙ መላእክት ጋር መጣና ተገለጠ። **ኢየሱስ** ከራሱ ጋር ዘጠኝ በጎችን እየመራ ነበር። **ኢየሱስ** ያመጣቸው በጎች ቁጥርና በጸሎት የሚተጉት ጦረኞች ቁጥር አንድ አይነት እንደሆነ አስተዋልኩ! *"እናንተ ሁላችሁ የእኔ በጎች ናችሁ። እኔ ሁሌም እናንተን እየተመለከትኳችሁ ነው፣ ስለዚህ አትጨነቁ።"*



የፓስተር ኪም ስብከት እየነደደ ነበር፣ እና እርሱ በቅዱስ እሳት ይናገራል። ኢየሱስ በፓስተሩ ስብከት በጥልቀት ተሳትፎ ነበር፣ እናም በታላቅ ደስታ ጮኸ፣ *"ታላቅ ሥራ፣ ፓስተር ኪም። ታላቅ ነገር እያደረክ ነው።"* **ኢየሱስ** ፊቱ እየበራ ፈገግ ብሎ ከፓስተሩ ጎን በመሆን ከፓስተሩ እኩል ይራመድ ነበር። ፓስተሩ ወደ ግራው ሲዞር፣ **ኢየሱስ** ወደ ግራ ይዞራል፤ እሱ ወደ ቀኝ ሲዞር፣ **ኢየሱስ**ም ወደ ቀኝ ይዞራል። ከዛ አስር መላእክት ተገለጡ። አንዱ ከተገለጠ መጽሐፍ ጋር ቆሞ በፍጥነት አንድ ነገር ይመዘግባል። ሌሎቹ መላእክት ጎርጓዳ ሣህኖች ተሸክመው ስብከቱን እየሰበሰቡ ፓስተሩን ከበውታል። አንዱ ጎድጓዳ ሣህን ሲሞላ፣ ቀጣዩ መልአክ ከሌላ ጎድጓዳ ሣህን ጋር ይመጣል፣ እናም ይህ ወደ ገነት ተሸክመውት ሲሄዱ ይቀጥላል። **ኢየሱስ** ተደሰተ፣ እና መላእክቱም ተደሰቱ።

ከስብከቱ በኋላ፣ በስተመጨረሻ በሕብረት የመጸለያ ሰዓት ነበር። እየጸለይን እያለ፣ ዘጠኙም የጸሎቱ ቡድን አባላት ሁላችንም ውጊያ እየተዋጋን ያለ ነው የሚመስለው። ወደ **ጌታ** በንስሐ(በጸጸት) እያለቀስን እያለ፣ እንባዎችና ላብ በላያችን ላይ ይመጣ ነበር።

ከዛ **ኢየሱስ** ስሜን እየጠራ ቀረበ። **ጌታ** ብዙ ቤተ ክርስቲያኖችን በማነጻጸር ተናገረ:- *"ቦንግ-ንዮ፣ ብዙ ቤተ ክርስቲያኖች ተኝተውና በሳምንቱም ምሽቶች የበራውን ቀይ ምልክታቸውን ይዘዋል፣ ግን <u>የጌታ ቤተ ክርስቲያን (The Lord's Church)</u> አባላት በጣም በትጋት ይጸልያሉ። አሁን እኔ እጅግ በጣም ደስተኛ ነኝ።"* ከዛ መላእክት በሶስት ቡድኖች ወደ ታች ወረዱ። አንድ፣ ሁለት፣ ሶስት፣ አራት፣ አምስት፤ ለተወሰነ ጊዜ ቆጠርኩ፣ ነገር ግን የሰልፋቸውን መጨረሻ ማየት አልቻልኩም፣ ስለዚህ አቆምኩኝ። ማለቂያ ሳይኖራቸው ወደ ታች መውረድ ቀጠሉና ዘጠኞቻችንም በጸለይንበት በመሠዊያው ፊት ቆሙ። እነሱ ጸሎቶቻችንን በወርቃማ ጎድጓዳ ሣህን ሰበሰቡና ወደ ሰማይ ወሰዷቸው እና ከዛ ተመለሱ። መላእክቱ ጸሎቶቻችንን ወደ **እግዚአብሔር** ወሰዱት። ከቅርብ ጊዜ ወዲህ ግን፣ የ**ጌታ** ቤተ ክርስቲያን አባላት ሌሊቱን ሙሉ እያመለኩና ራሳችንን በ ጸሎት እያተጋን በመሆኑ፣ በጣም ብዙ የሚሰሩት ስለሰጠናቸው መላእክቱ አመሰገኑን።

**ኢየሱስ**ም አለ:- *"በትጋት ወደ ጌታ እየጠራችሁ እና ቀንና ሌሊት በማምለካችሁ፣ ሰማያዊው አባት፣ እኔም ራሴ፣ እና መንፈስ ቅዱስ በአላማችሁ ቆራጥነት ተደንቀናል። በመሬት ላይ እንደናንተ አይነት ቤተ ክርስቲያን የሚገኘው በጣም*

*በጥቂቱ ነው።"* የሰማይ አባት እኛን እንዲህ ጠየቀን:- *"ምን ልሰጣችሁ እችላለሁ?"* ከዛ አባትየው **ኢየሱስ**ን ጠየቀው፣ *"የኔ ልጅ፣ ምን ማድረግ እንዳለብኝ ታስባለህ?"* **ኢየሱስ** መለሰ፣ *"አባቴ፣ እንደፈቃድህ አድርግ።"* **መንፈስ ቅዱስ** በቅዱስ እሳት፣ በዘይት፣ እና በሰማያዊ(በሰማይ) ስጦታዎች ቀባን። አባትየው እንዲህ አለ:- *"ሊፓስተሩ ሚስት፣ ካንግ, ሀዩን-ጃ፣ እኔ በተለየ መልኩ በኃይለኛው በሚነደው የመንፈስ ቅዱስ እሳት እና በሽተኞችን የመፈወስ ብቃት ልቀባት እፈልጋለሁ፣ እና እሷ መንፈሳዊውን ዳንስ በደፋርነት እንድትደንስ እፈልጋለሁ።"*

የፓስተሩ ሚስት በመንፈሳዊ ሁኔታ መደነስ ስትጀምር፣ ሁሉም በአግርሞት ተመለከታት። ከ**መንፈስ ቅዱስ** መሪነት በታች መደነስ ስትጀምር ፊቷ ወደ ቀይ ተለወጠ።

**እግዚአብሔር** በድንገት እኔ ከውሀ በታች ያለሁ በሚመስል ቦታ ውስጥ ገፋኝ፣ አካሌና እግሮቼ በራሳቸው አእምሮ የሚንቀሳቀሱበት የሚመስል ቦታ። ከጥቂት ጊዜ በኋላ የ**ጌታ** ድምጽ እንዲህ ሲል ሰማሁት፣ *"እኔ በኃይለኛው በሚነደው እሳት አጠምቅሻለሁ።"* ዘይት ውስጥ የተወረወርኩ ያህል ተሰማኝ፣ ከዛ ወዲያውኑ አካሌ እንደ እሳት ኳስ ተሰማኝ።



ከቆይታ በኋላ፣ **ኢየሱስ** በኮሪያ ስላሉ ቤተ ክርስቲያኖች ማውራት ጀመረ። በቁጣ ቅላጼ እርሱ እንዲህ አለ፣ *"አንድ ቤተ ክርስቲያን ትልቅና መስቀሉ እያበራ ባዶ ቦታ ያሉት ብቻ ከሆነ ምንድነው ጥሩነቱ? የጠፉትን ነፍሳት እንዲያድኑ ካህናት መሪዎችን እኔ መርጫቸዋለሁ፣ ነገር ግን እነሱ ጸሎት አንሷቸዋል፣ እና ያ ልቤን እየሰበረው ነው።"*

ከቆይታ በኋላ፣ **ኢየሱስ** እጄን ይዞ:- *"በንግ-ንዮ፣ ከእኔ ጋር ወደ ገነት ነይ፣"* ሲለኝ እኔ ቅዱሱን ዳንስ እየደነስኩኝና በልሳኖች እየጸለይኩኝ ነበር። የ**ኢየሱስ**ን እጅ እንደያዝኩኝ፣ ወዲያውኑ ነጭ ልብስ ለብሼ ነበር፣ እና ከ**ኢየሱስ** ጋር አየር ውስጥ እየበረርኩ ነበር። ወደ ላይ ከፍ እንዳልኩ፣ መሬት እያነሰችና እያነሰች መጣች። ዩኒቨርሱ (the universe) በጣም ያምር ነበር። እኛ ለተወሰነ ጊዜ በረርን፣ ከዛ በኋላ ጋላክሲ (የከዋክብት ክምችት) ጋር ደረስን። ጋላክሲውን ስናልፍ፣ በድጋሜ ጨለማ እየሆነ መጣ፣ እና ሁለት መንገዶች አየሁ። በቀኝ በኩል ባለው መንገድ ሄድን፣ ስለዚህ እንዲህ ብዬ ጠየኩ፣ *"**ጌታ** ሆይ፣ የግራው መንገድ ወደ የት ነው የሚመራው?"* ወደ ሲኦል እንደሚመራ እርሱ ነገረኝ። ለተወሰነ ጊዜ መንገዱ ላይ ያለን ይመስላል። በድንገት በጣም ኃይለኛ ብርሃን ተገለጠ፣ ከብርሃኑ ሀይለኛነት የተነሳ ዓይኔን መግለጥ አልቻልኩም ነበር።

መንግሥተ ሰማይ በከዋክብት ተሞልታለች። በምድር ያሉ ሰዎች ብዙ ጊዜ ገነት የሚለውን ቃል ይላሉ፣ ነገር ግን ያየሁት በምድራዊ ቃላቶች አይገለጽም። *"እንዴት ሊሆን ይችላል? ይህ እንዴት ሊሆን ይችላል?"* ብዬ ጠየኩ። ሰዎች መንግሥተ ሰማይ ምን እንደሚመስል ሙሉ ለሙሉ ሊያስቡ (ሊያውቁ) አይችሉም። ብዙ መላእክት ሰላምታ አቀረቡልኝና ተቀበሉኝ። **ኢየሱስ** እንዲህ አለ:- *"አንቺ ወስነሽ እና ቤተ ክርስቲያን በትጋት ለመገኘት ራስሽን አስገብተሻል፣ ስለዚህ በገነት ያለውን ቤትሽን ላሳይሽ እፈልጋለሁ። እኔን ተከተይኝ።"* ብዙ መላእክት አንድ ነገር እየገነቡ ተመለከትኩ። **ኢየሱስ**፣ *"ይህ የአንቺ ቤት ነው።"* ብሎ ነገረኝ። ተመለከትኩ፣ ነገር ግን ምንም ቤት የለም ነበር። ጥልቅ የሆነ መሠረት ብቻ ነው ያየሁት። መላእክቱ ስራቸውን ለማከናወን ወርቅ እየተጠቀሙ ነበር። **ኢየሱስ** እንዲህ አለ:- *"በጥቂት ቀናት ቤትሽ ወደላይ ይወጣል። ተስፋ የቆረጥሽ አትሁኝ፣ ነገር ግን በትጋት ጸልዩ እና በታማኝነት ኑሪ። ሰይጣንን አምልከሽ እና ብዙ ሰዎችን ወደ ከንቱ ስሜት መርተሽ ነበር። ነገር ግን በእኔ ለማመን እና ቤተ ክርስቲያን በትጋት ለመገኘት ቁርጥ ሀሳብ አድርገሻል።"* **ኢየሱስ** እንዲህ አለ፣ *"ላሳይሽ የምፈልገው አንድ ቦታ አለኝ፣ ስለዚህ እኔን ተከተይኝ፣"* እናም እርሱ ወደ ሌላ ቦታ መራኝ። *"የእኔ ተወዳጅ በንግ-ንዮ፣ የሀብቱን ግምጃ ቤት እና ወንጌልን ለአንቺ ለመስበክ ሀላፊነት ያለባቸውን ሰዎች ቤት፣ የቤተ ክርስቲያንሽ ፓስተር፣ ኪም, ዮንግ-ዱ፣ እና የእሱ ሚስት ካንግ, ሀዩን-ጃ። በጥንቃቄ ተመልከቺ። የመሬት አንድ ሺህ ፎቅ ህንጻ በመንግሥተ ሰማይ ላለው አንድ ህንጻ ፎቅ ይነጻጸራል፣ እና በመንግሥተ ሰማይ ያለው ሁሉም ነገር ውሱን በሆነው በሰዎች መዝገበ ቃላት ሊገለጽ አይችልም።"*

ከዐይኖቼ ፊት አንድ በጣም ረጅም ህንፃ ነበረ፣ የሚፈነጥቀው ብርሃንም በጣም ኃይለኛ ስለነበር ጭንቅላቴን ማንሳት አልቻልኩም። *"ይህ የፓስተር ኪም, ዮንግ-ዱ ቤት ነው።"* **ኢየሱስ** ቀኝ እጁን ወደላይ አነሳና ወዲያውኑ በመንግሥተ ሰማይ ያለውን የፓስተሩን የሚያምር አዲስ ቤት በግልጽ ማየት ቻልኩ። ከዛ ጌታ፣ እንዲህ አለ፣ *"አሁን፣ የፓስተር ኪምን የሀብት ግምጃ ቤት እንይ።"* ከቤቱ እስከ ግምጃ ቤቱ ድረስ ያለው ርቀት በግምት ከሶስት እስከ አራት የባስ ማውረጃዎችን (ማቆሚያዎችን) ያህላል፣ በንጽጽር። የፓስተሩ የሀብት ግምጃ ቤት በመቶዎች በሚቆጠሩ መላእክት በከባዱ እየተጠበቀ ነበር፣ ስለዚህ መግባት አልቻልንም። **ኢየሱስ** ሲቀርብ፣ ጠባቂ መላእክቶቹ ክንፋቸውን ወደታች አደረጉና ቀጥ ብለው ቆሙ እናም በፊቱ አጎንብሰው እጅ ነሱ። በመንግሥተ ሰማይ በእያንዳንዱ የሀብት ግምጃ ቤት ለመግባት የኢየሱስን ፈቃድ ይጠይቃል። ከግምጃ ቤቱ የሚወጡት የሚፈነጥቁት ቀለሞች፣ የሚያስገርሙ መልኪ ናቸው። *"ዋው፣ ፓስተር ኪም በጣም*

*ደስተኛ ይሆናል፣"* አልኩኝ። በሀብቱ ግምጃ ቤት ውስጥ ሊቆጠሩ የማይችሉ ብዙ መላእክት ከመሬት የሚመጡትን ሁሉንም የፓስተሩን እቃቆች በማከማቸት ባተሌ (ሥራ በዝቶባቸው) እየተጉ ነበር።

[የፓስተሩ እቃዎች ከመሬት መጡ ሲባል ምድራዊ እቃዎችን ወይም ቁሶችን ሳይሆን፣ ፓስተሩ **ለእግዚአብሔር ኢየሱስ ክርስቶስ** የሚያደርጉት አገልግሎት ሁሉ ያ እንደ ግብአት ወደ ሰማይ ይወሰዳል፣ ማለትም አምልኮተ እግዚአብሔር ኢየሱስ **ክርስቶስ** ማካሄድ፣ **የእግዚአብሔርን ኢየሱስ ወንጌል** መስበክ፣ የተቸገሩትን መርዳት፣ **ኢየሱስ**ን መከተል ማመን፣ እንደ **ኢየሱስ** ቃል መኖር፣ **የእግዚአብሔር አብን ፈቃድ** ማድረግ፣ ላላመኑት ስለ **ኢየሱስ ክርስቶስ** እውነተኛ መድኃኒትነትና ጌትነት ወንጌልን መስበክ፣ እንደ ኢየሱስ ቃል መኖር፣ በጸሎት ከኢየሱስ ጋር መትጋት፣ መጾም በ**ኢየሱስ** ሆኖ፣ መጽሐፍ ቅዱስ ማንበብ እና እንደ **ኢየሱስ ቃል** ሌሎችም እንደ ቃሉ]

የፓስተሩ ሀብት በመከማቸት ላይ ይገኛል (ቀጥሏል)። **ኢየሱስ**ን ጠየኩት፣ *"ለምንድን ነው የፓስተር ኪም ቤት ትልቅ የሆነው እና ለምንድን ነው እሱ ብዙ ሀብት ያለው?"* **ጌታ** መለሰልኝ:- ***"ፓስተር ክም, ዮንግ-ዱ፣ ታማኝ እርምጃውን በጊዜ ነው የጀመረው እና ሁሌም ይጸልይና እኔን በትጋት ያገለግለኛል።"*** **ኢየሱስ** እንዲህ አለ:- ***"ዛሬ ያለን ሰዓት ይህ ሁሉ ነው፣ ስለዚህ በሚቀጥለው እዚህ ስትመጪ ተጨማሪ እንይ።"*** እርሱ ወደ ቤተ ክርስቲያን መልሶ አመጣኝ። **ኢየሱስ** እኔን ከመተዉ በፊት የመጨረሻ አንድ ነገር አለ፣ ***"መስቀል ላይ የሞትኩ ጊዜ፣ ብዙዎች ድጋሜ እንደማልኖር አምነው ነበር። እነሱ*** [ብዙዎች] ***እኔን ማመን አቆሙ፣ ወደ ቤተ ክርስቲያን መሄድ አቆሙ፣ እና አሁን ሌላ ነገር እያደረጉ ነው፣ አለማዊ ነገሮች።"***

# ==== ቀን 7 ====

**ኪም, ጁ-ኢዩን:**

ለአንድ ሰዓት ያህል በልሳኖች ጸለይኩኝ፣ በድንገት አንድ ደማቅ ብርሃን በራ። ከዛ **ኢየሱስ**፣ ነጭ ልብስ ለብሶ፣ ከአይኖቼ ፊት ተገለጠ። **ኢየሱስ** ቡናማ ጸጉር ነበረው እና የሚያንጸባርቅ ነጭ ልብስ (ከአንድ ወጥ እንደተሰራ ልሙጥ ልብስ የሚመስል) ለብሶ ነበር። እርሱ ስሜን ጠራው፣ ***"ጁ-ኢዩን፣ የእኔ ተወዳጅ ጁ-ኢዩን፣ እኔ አፈቅርሻለሁ።"*** **ኢየሱስ** እየተናገረኝ እያለ ወደኔ ተጠጋ። በጣም ተደንቄ ነበር እናም እንዲህ አልኩ፣ *"አንተ በእውን **ኢየሱስ** ነህ? ዋው **ኢየሱስ**፣ በእውነት እኔ አፈቅርሃለሁ። አንተ ግሩም(አስደናቂ) ነህ።"* በመደነቅ ተሞልቼ ነበር ምክንያቱም ምን ማድረግ እንዳለብኝ አላውቅም ነበር። **ኢየሱስ** እንደሚያፈቅረኝ እየተናገረ ከፊቴ ቁጭ አለ። እኔም በደስታ እንዲህ አልኩ፣ *"**ኢየሱስ**፣ በእውነት አፈቅርሃለሁ።"* እና እርሱ እንዲህ መለሰ:- ***"አዎ፣ እኔም እንዳንተው በጣም አፈቅርሻለሁ።"*** **ኢየሱስ** እንዲህ አለ፣ ***"በትጋት ጸልዪ፣ እና እኔ ራሴን ላንቺ እገልጥልሻለሁ። እኔ ወደ መንግሥተ ሰማይ እወስድሽና ዙሪያውን አሳይሻለሁ። ስለዚህ፣ በትጋት ጸልዪ፣"*** እና እርሱ ተሰወረ።

**ኢየሱስ**ን ባላየሁት ጊዜ፣ በሙሉ ሀይሌ በልሳኖች መጸለይ ጀመርኩ። በድንገት አንድ እንግዳ ነገር ከፊቴ መጣ፣ ወደኔ እየሮጠ ነበር። የሁለቱም አይኖቹ ጫፎች በትንሹ ተቆራርጧል፣ እና የቀኝ አይኑ ላይ የ X ቅርጽ አለው። ይህ ሰይጣን በሰንበሮች ተሸፍኗል። እኔም እንዲህ ብዬ ጮህኩ፣ *"በ**ኢየሱስ** ስም፣ ከእኔ ርቀህ ተወገድ።"* ሰይጣኑ ጠፋ። እኔ መጸለይ ቀጠልኩ፣ ዐይኖቹ ከድመት ዐይኖች የጠበበ አንድ ነገር ከፊቴ ተገለጠ። እንደ የሌሊት ወፍ ክንፎች አይነት ክንፎች እና ወደ ውጭ የወጡ የሚያስፈሩ ሹል ጥርሶች ነበሩት። ሊያስፈራራኝ በፍጥነት ወደኔ መጣ፣
ነገር ግን በ**ኢየሱስ** ስም አሸነፍኩት።



ከዛ፣ በተወሰነ መልኩ የሚታወቅ ሰይጣን መጣ፣ እና ይህንን ከዚህ በፊት የት እንዳየሁት ለማወቅ ፈለግሁ። ስታርክራፍት (Starcraft) ከሚባለው የኮምፒዩተር ጌም ላይ ያየሁት ገፀ ባህርይ እንደሆነ ተገነዘብኩ። ይህች ሴት ሰይጣን ወደኔ ሮጠች። አፍጥጣ እያየችኝ ልታስፈራራኝ ሞከረች። የኢየሱስን ስም ስጠራ በፍጥነት እንደሚጠፉት ክፉ መናፍስት ሳይሆን፣ ይህች ሴት ሰይጣን በቀላሉ አልሄደችም። በተደጋጋሚ ከጮህኩኝም በኋላ እንኳ፣ ትንሽ እንቅስቃሴ አላደረገም፣ እናም የእውነት እየፈራሁ ነበር። በአስቸኳይ ከፓስተር ኪም አጠገብ ከመስበኪያው ቀጥሎ ሄድኩና መጸለይ ቀጠልኩ። ፓስተር እጄን ያዘና ወደላይ አነሳው፣ ከእኔም ጋር ጸለየ እና ከዛ ብቻ ነው ሰይጣኑ የሄደው።

# ==== ቀን 8 ====

**ፓስተር ኪም, ዮንግ-ዱ:**

በቆራጥነት የማህበር ጸሎት ከጀመርን አንድ ሳምንት ሆኗል። መንፈሳዊ ውጊያችን ኃይለኛ እየሆነ መጥቷል፣ ስጋዊ ፈተናዎቻችንም በየቀኑ ቀጥለዋል። አንድ በአንድ፣ የእያንዳንዱ የጸሎት ኃይለኛ ወታደሮች መንፈሳዊ ዐይን (የማየት ኃይል) ተከፈተ እና በ**መንፈስ ቅዱስ** ተሞልተው ነበር። የሰይጣን ኃይሎች ከዛ ኃይል የተቀላቀለበት የማጥቃት እንቅስቃሴ አደረጉ። የንዴታችንን መጠን እየፈተኑ፣ ብዙ ግላዊ ሁነቶች ተነሱ። በመጀመሪያው ቀን፣ ከመኪናዬ ጎማዎች አንዱ በጣም ከፉ በሆነ መልኩ የተቆረጠ ስንጥቅ ነበረው። በቀጣዩ ቀን የፊተኛው ጎማ ሌላ በትልቁ ተቀርጧል። በዚህ ሁነታ በጣም ፈርቼ ነበር። ቢሆንም፣ ለ**እግዚአብሔር** አላማረርኩም፣ በተቃራኒው ግን በምስጋና ልብ *"ሃሌ ሉያ"* ብዬ ጮህኩኝ። በቀጣዩ ቀን መኪና የሚጎትት ትልቅ መኪና መኪናዬን ወሰዳት። ይህ በእርግጥ እኔን ከከፍታ ላይ ለመገፍተር የቀረበ ነበር፣ ነገር ግን ሚስቴና የቤተ ክርስቲያናችን አባላት ይህን አስታወሱኝ፣ *"ፓስተር፣ በዚህ ውስጥ ተቋቁመህ መቀጠል አለብህ።"* ከቆይታ በኋላ፣ አንድ ሰው የመኪናውን መብራቶች ሰበራቸው፣ እና ከዛ ቀን ቀጥሎ ባለው ቀን አንድ ሰው በሹል እቃ የመኪናዋን ጎን ፋቀው።

የቤተ ክርስቲያኑ አገልግሎት **መንፈስ ቅዱስ** በመራበት መንገድ በጥሩ ሁኔታ ቀጠለ። እስከዛ ድረስ በቤተ ክርስቲያኑ ውስጥ ያለው ርዕስ እንዲህ ይነበባል፣ "የ**መንፈስ ቅዱስ**-ምልአት ከፍተኛው ሰዓት፣ (The **Holy Spirit**-filled climatic hour,)" ግን ያ በዚህኛው ተተካ፣ "የእውነት **መንፈስ ቅዱስ**-የሚመራው አገልግሎት። (A real **Holy Spirit**-led service.)"

አምልኮቱ፣ ጸሎቱ፣ ስብከቱ፣ እና የመስዋዕት ስርዓቶች ተወግደው ነበር፣ አምልኮት፣ ጸሎት፣ ስብከቱንና እወጃውን እንዲመራ በ**መንፈስ ቅዱስ** አመራር ላይ ተደግፈን ነበር። በታቀደለት ጊዜ ውስጥ ለመፈጸም የሚያስገድድ ምንም ስለሌለ፣ ስብከቱ ከተያዘለት ጊዜ ውጪ ሊካሄድ ይችላል።

በእኛ የሙሉ ሌሊት የጸሎት ጊዜያት እያንዳንዱ የጸሎት ኃይለኛ ወታደር የኢየሱስን መገኘት ያያል፣ ስለዚህ እነሱ ድካም አይሰማቸውም፣ ምንም እንኳ አገልግሎቱ እስከ ቀጣዩ ቀን ንጋት ድረስ ቢቀጥልም። እኛ ሁሌ ንቁ ነን፣ እና ሰይጣን ያለማቋረጥ ስለሚያጠቃ መከላከያችንን የማውረድ ምንም ሰዓት የለም።

**ኪም, ጁ-ኢዩን:**

**ኢየሱስ** እንዲህ እያለ እየቀረበኝ ሳለ በልሳኖች እየጸለይኩ ነበር፣ *"ጁ-ኢዩን አፈቅርሻለሁ።"* እርሱ ቀጠለ:- *"ጁ-ኢዩን፣ በትጋት ጸልዪ፣ እና እኔ እጅሽን እይዝና ወደ መንግሥተ ሰማይ እመራሻለሁ። ያለማቋረጥ ጸልዪ፣ መንግሥተ ሰማይን አሳይሻለሁ። ተረዳሽ?"*



ከዛ በኋላ በዛ ምሽት፣ ከፉ አጋንንቱ በቡድን መጡ። አንዱ ልክ እንደ የሌሊት ወፍ ክንፎቹን እያውለበለበ ተገለጠ፣ እራሱ ላይ ሁለት ትንንሽ ቀንዶች እና እንደ ድመት አይነት ዐይኖች አሉት። ሰይጣኑ አፎቹ በስፋት ተከፍተው ሞቃት የሚገማ ፈሳሽ ከአፉ እየወጣ ወደኔ እየበረረ መጣ። ዐይኖቹ እንደደም ቀይ ናቸው። እኔ ጮህኩ፣ *"በ**ኢየሱስ** ስም፣ እኔ አዝሃለሁ አንተ በጣም ቆሻሻ እና ቆሻሻ ሰይጣን: ከእኔ ሽሽ።"* በዛ ትእዛዝ፣ ጠፋ። ከጥቂት ጊዜ በኋላ፣ ትንንሽ ዐይኖች ያሉት ሰማያዊ ፊት ሰይጣን ቀረበኝ። እኔ ፈርቼ ነበር እና በሁሉም አካሌ ላይ የዝይ እብጠት ነበር። እንዲህ ብዬ በኃይል ወደውጭ ጮህኩ፣ *"በ**ኢየሱስ** ስም፣ ከእኔ ሽሽ።"* ነገር ግን ይህ ሰይጣን አልተንቀሳቀሰም። በመንቀሳቀስ ፈንታ በቁጣ እኔ ላይ አፈጠጠብኝ። በጣም ጮህኩ እና በፍርሃት ተሞልቼ ነበር፣ ከአጠገቤ ተቀምጣ የነበረችው እህት ቤይክ ቦንግ ንዮ በጩኸት ተቀላቀለችኝ፣ *"በ**ኢየሱስ** ስም፣ ከእኛ ራቅ!"* የዛኔ ብቻ ነው የሸሸው።

አንድ ግዙፍ ቀይ ድራጎን ወደ እኔ መብራር ሲጀምር ጸሎቴን ቀጠልኩ። ዐይኖቹ አረንጓዴ ነበሩ። ረጅም፣ ሹል ቀንዶች ከጭንቅላቱ ወጥተዋል። በአፍንጫው ቀዳዳዎች ውስጥ ጭስ ነበረ። በፍጥነት ወደኔ መጣ፣ እኔን ከነ ሕይወቴ ሊውጠኝ ይመስላል። አልተንቀሳቀስኩም። **በኢየሱስ ስም** በትጋት በልሳኖች እየጸለይኩ፣ መሬቴ ላይ ቆሜያለሁ፣ እና በድንገት ሰይጣኑ ጠፋ። መጥፋቱ በጣም የሚያረካ (የሚያስደስት) ስሜት ነበር። ከዚህ ልምድ በፊት የኢየሱስን ስም ኃይሉንና ከፍተኛነቱን አልተገነዘብኩም። በቀጣይ ሰዓት (ጊዜ)፣ አንድ በጣም የሚያስጠላ፣ በጣም ክፉ፣ እና አጽም ፊት ሰይጣን እየተንከተከተ (በማይረባ አሳሳቅ) እያፌዘብኝ ከፊቴ ፊት ለፊት መጣ። ሰይጣኑን ለማባረር አንድ ጊዜ በድጋሜ የ**ኢየሱስ**ን ስም በመጠቀም በልሳኖች ጸለይኩኝ።

ከቆይታ በኋላ፣ **ኢየሱስ** መስቀል ላይ ተሰቅሎ እያሰብኩኝ ነበር፣ እርሱም (**ኢየሱስ**) እያበረታታኝ እና ***"ጁ-ኢዩን፣ ጥቂት ትንሽ ተጨማሪ፣ ለተወሰነ ጊዜ ረዘም ያለ ጸልዩ።"*** እያለ ተገለጠ።

# ==== ቀን 9 ====

**<u>ሊ, ሀከ-ሱንግ:</u>**

የሰይጣን የተጠናከረ(የተተኮረ) ጥቃት ተጀመረ። ጁ-ኢዩን ስለሱ የነገረችኝ ቀይ ድራጎን ከፊቴ ተገለጠ። የእሱ ግዙፍ አካል አስፈራኝ። ቀይ ዐይኖች ነበሩት፣ እና ጥቁር ጭስ ከአፍንጫው ቀዳዶች ውስጥ በፍጥነትና በኃይል ይወጣ ነበር። ጥርሶቹ እንደ ቀንዶች ሹል ነበሩ፣ ጥፍሮቹ ወደ ውጭ ይጠቁማሉ እና ጭራው በሚያስፈራ መልኩ ረጅም ነበር። ቢሆንም፣ እኔ በድፍረት ጸለይኩ፣ እና ድራጎኑ በድንገት ጠፋ። ከጥቂት ጊዜ በኋላ፣ አንድ ሴት ሰይጣን እየጮኸች ተገለጠች፣ "*ሂ-ሂ-ሂ!*" አፏ የተኩላ ጥርስ በሚመስል ጥርሶች የተሞላ ነው። በተጨማሪ፣ ከኋላዬ ወታደሮች በታላቅ የቁጣ ጫጫታ በውጊያ ጫማዎች በወታደራዊ አካሄድ ሲራመዱ መስማት ጀመርኩ። እና ከአጭር ጊዜ በኋላ ጥቁር ጥላዎች ዙሪያዬን ከበውኝ ነበር። የሰይጣን ጫጫታ እና የወታደሮች የቁጣ እርምጃ አስፈራኝ፣ ስለዚህ ማልቀስ ጀመርኩ፣ *"**ጌታ** ሆይ፣ እርዳኝ። እባክህን እርዳኝ!"* ወደ**ጌታ** እየጮህኩኝ እያለ **ኢየሱስ** በደማቅ ብርሃን ተገለጠ። **ኢየሱስ** እንደተገለጠ ክፉ መናፍስቶቹ ተሰወሩ (ጠፉ)። **ኢየሱስ** እጄን ያዘ፣ እና እኔ ከ**ኢየሱስ** ጋር ዘመርኩ እና ደነስኩ።

ከቆይታ በኋላ፣ **ኢየሱስ** ጠራኝ:- ***"የእኔ ተወዳጅ ሀከ-ሱንግ፣ መንግሥተ ሰማይን መጎብኘት ትፈልጋለህ?"*** እርሱ እጄን እንደያዘ፣ አካሌ ነጭ ካባ ለበሰ። አየር ላይ ተንሳፈፍኩ፣ እና እየጠበቁን ወዳሉት ወደ ሰማያውያን መላእክት በረርን። በዚህ ደማቅ ብርሃን መገኘት እራሴን በአግባቡ ማንሳት አልቻልኩም። መንግሥተ ሰማይ በከዋክብት የተሞላ ቦታ ተብሎ ሊገለጽ ብቻ ይችላል። እያለምኩ ያለ አርጌ ነበር ያሰብኩት፣ ነገር ግን መንግሥተ ሰማይ ከመሬታዊው አለም በላይ እውን ነው። መንግሥተ ሰማይ ሁሉ በወርቅ ተሸፍኗል። ከዛ ብርሃን የማይፈነጥቅበት ምንም ቦታ የለም። ብዙ መላእክትና ቅዱሳን በስራ ተወጥረው (ብዙ የሚሰራ ሥራ ኖሯቸው) ይንቀሳቀሳሉ፣ እና መላእክት በደስታ ሰላምታ አቀረቡልኝ። እኔም እንዲህ አልኩ፣ *"**ኢየሱስ**፣ እዚህ ለእኔ ቤት እንዳለ ማወቅ እፈልጋለሁ።"* ከዛ **ኢየሱስ** ቤቴ ወደነበረበት አብረውኝ እንዲሄዱ ሁለት መላእክት ላከ። ቤቴ ትልቅ አልነበረም፣ ግን ግርግዳዎቹ በወርቃማ ጡቦች ተሰርቷል። በተለያዩ አበባዎች የተሞላ ግዙፍ የአበባ መናፈሻ አየሁ። ድንገታዊ የሆነ መናፈሻው ውስጥ ዘሎ የመግባትና የመንከባለል አስቸኳይ ሀሳብ ነበረኝ። የአበቦቹን ጣፋጭ መዓዛ ሳሸት፣ በደስታ ተሞላሁና እንደ ልጅ ወደላይና ወደታች ዘለልኩ።

**<u>ሊ, ዩ-ክዩንግ:</u>**

በልሳኖች እየጸለይኩኝ እያለ አንድ ሰይጣን ቀረበኝ። በቀይ ዐይኑ ላይ በX ምልክት የስፌት ጭረት ነበር እና ግራ ዐይኑ የ<u>ራኮን</u>ን ጥቁር ዐይን ልጥፍ ይመስላል። ወንድ ሰይጣን ይመስላል፣ እና እኔ እንዲህ ብዬ ጮህኩ፣ *"በ**ኢየሱስ** ስም፣ ከኔ ሽሽ።"* ከቆይታ በኋላ፣ የሌሊት ወፍ ክንፎች ያሉት አንድ ሰይጣን ቀረበኝ፣ "*እኔን እንዲህ የምታስቆጪኝ ምን የተሳሳተ ነገር አድርጌብሽ ነው?*" ተማጸነ፣ "*አንዴ ብቻ አንቺ ውስጥ ገብቼ እንድወጣ ከፈቀድሽልኝ በፍፁም ድጋሜ አልመጣም።*" እኔም መለስኩ፣ *"አንተ--አንተ ቆሻሻ ሰይጣን፣ በኢየሱስ ስም፣ ከእይታዬ ተወገድ (ውጣ)!"* በዛ ትእዛዝ፣ ጠፋ (ተሰወረ)። ከዛ በኋላ፣ ከሶስት ወይም ከአራት የተለያዩ ሰይጣኖች ጋር ተዋጋሁ። ከዛ በድንገት፣ ጣፋጭ-የሚሸት መዓዛ በዙሪያዬ አሸተትኩ። **ኢየሱስ** መጣና ስሜን ጠራ:- ***"የእኔ ተወዳጅ ዩ-ክዩንግ፣ እጆችሽን ስጭኝ።"*** ስለዚህ እጆቼን ዘረጋሁ፣ እና **ኢየሱስ** በሞቃትና በተረጋጉ እጆቹ እጆቼን ያዘ። እኔም እንዲህ አልኩ፣ *"**ኢየሱስ**፣ ትከሻዬ ባስከፊ ሁኔታ እያሳመመኝ ነው።"* እና **ኢየሱስ** እጆቹን ትከሻዎቼ ላይ ሲያኖር ህመሙ እያነሰ ሄደ(ጸጥ አለ)። **ኢየሱስ** ለእያንዳንዱ የጸሎት ኃይለኛ ወታደር ቅጽል ስም ሰጥቷል። ያ ታላቅ አዝናኝ ነበር። **ኢየሱስ** እኔን "ስፔክል ፌስ (ጠቃጠቆ ፊት)" ብሎ ጠራኝ።

ምክንያቱም ፊቴ ላይ ብዙ ጠቃጠቆዎች አሉብኝ። የጁ-ሊዩን ስም “ሴሳሚ (ሰሊጥ)” ወይም “ፍሬክልስ (ጠቃጠቆ)” ነው። ምክንያቱም እሷ በጠቃጠቆዎች ተሸፍናለች።


ከቆይታ በኋላ፣ ኢየሱስ አጽናናኝ ምክንያቱም የቤተሰብ አባሎችን በሲኦል ውስጥ ስላየሁ ሁሉም ህመም ውስጥ አሳልፌ ነበር:- *“የእኔ ተወዳጅ ዩ-ክዩንግ፣ ቅድመ አያትሽን በሲኦል ካገኘሽ በኋላ ብዙ አልቅሰሻል።”* **ጌታ** ይሄንን አስታወሰኝ፣ *“ዩ-ክዩንግ፣ ሲኦልን እንድትጎበኚ ስወስድሽ፣ ለማንም እጅሽን መስጠት የለብሽም፣ ተወዳጅሽ ቅድመ አያትሽ ብትሆንም እንኳ፣ በዛ ቦታ በፍፁም የማንንም እጅ መያዝ የለብሽም።”*

ከቆይታ በኋላ፣ **ኢየሱስ** በድጋሜ ሲኦልን እንድጎበኝ ወሰደኝ። በዚህ ጊዜ በቅርብ የሞተውን አባቴን እና የ26 ዓመቱን ታናሽ ወንድሜን አየሁ። እሱ መርዝ በመብላት እራሱን አጠፋ። ሁለቱም እራቁታቸውን ነበሩ። ዐይኖቻቸው ከዐይኖቼ ጋር ተገናኙ (ተገጣጠሙ)። *“ታላቅ እህቴ፣ ቦንግ-ንዮ፣ እዚህ እንዴት መጣሽ? ይህ ላንቺ ቦታ አይደለም፣ ትልቋ እህቴ፣ ወደጌታ ጸልዩ። ፍጠኚና እኔን እንዲያወጣኝ ከእርሱ ጋር ተማጸኚ። ወደ መንግሥተ ሰማያት እንድሄድ እርጂኝ። አሁን!”* ከነ እንባውና መማጸኑ፣ ወንድሜ የሚፈላ ፈሳሽ ወዳለበት ማሰሮ ውስጥ ተወረወረ። እየፈላ እንደሆነ መስማት ችያለሁ።

ወጣት ልጅ ከነበርኩ ጀምሮ፣ አባቴ ንቆኝ ነበር፣ እና ያ ጥላቻ በዓመታት እየገነነ መጣ። ምድራዊ አባቴ እንዲህ አለ፣ *“ቦንግ-ንዮ፣ እየኖርኩ እያለ አሁን በጣም የምጸጸትባቸው በጣም ብዙ የንቀት ነገሮችን አድርጌያለሁ። አሁን እዚህ ያለሁት ለዛ እንደሆነ እገምታለሁ። እኔ ከልቤ አዝኛለሁ።”* እኔ **ኢየሱስ**ን ጠየኩት፣ *“**ጌታ** ሆይ፣ አባቴ ለምን እዚህ መጣ?”* እርሱም መለሰ:- *“አባትሽ በጣም(በትልቁ) ሀጢአት ሰርቷል። እሱ በእኔ አላመነም፣ ግን እሱ በተጨማሪ አንድም ቀን ሳያቋርጥ ይቆምራል። እናትሽ ወንድምሽን እርጉዝ ሆና እያለ እና ልጁ በጤናማነትና በተፈጥሯዊ መንገድ ሊወለድ አንድ ወር ብቻ ሲቀረው፣ አባትሽ እናትሽን ሆዷን በጡቻ በመምታት ያን የተከበረ ህይወት በሆድ ውስጥ እያለ ቀጠፈው። ልጁ ሆድ ውስጥ እያለ በአእምሮ መዛባት ተሰቃየና ሞተ። አባትሽ በተጨማሪ በህይወት የነበረን አንድ ልጅ ከነሕይወቱ ተራራ ላይ እንድትቀብሪ አስገድዶሻል። ስለዚህ አስቀድመሽ ኢታውቂም? እንደዚህ አይነት አስከፊ ሀጢአት ከፈጸመ በኋላ፣ እርሱ በፍጹም ሀጢአቱን አልተናዘዘም(ንሰሃ አልገባም) ወይም ይቅርታ አልጠየቀም። እሱ እዚህ በሲኦል መሆኑ ትክክል ነው።”* የኢየሱስ የድምጽ ቃና በቁጣ ተሞልቶ ነበር።

አውቀው የነበረ ሌላ ፊት አየሁ፣ የታናሿ እህቴ የህግ እናት ነበረች። እኔ ወደመሬት (ምድር) ስመለስ፣ የህግ ሴት ልጇ እና ቤተሰቦቿ **በኢየሱስ ክርስቶስ** እንዲያምኑ፣ በትጋት እንዲጸልዩ፣ እና ሲኦልን እንዲያዩ፣ ስለዚህ ሁሉም ወደ መንግሥተ ሰማያት እንዲሄዱ እሷ በቅንነት ጠየቀች። እሷ እንዲህ አለች፣ *“እኔ በእርግጥ ሲኦል እንደነበር፣ ወይም እዚህ ምን ያህል ሞቃትና አሰቃቂ(መጥፎ) እንደሆነ አላውቅም ነበር። አንድ ጊዜ በቤተ ክርስቲያን የዲያቆንነት ርዕስ(ስም ማዕረግ) ይዜ ነበር፣ ነገር ግን በፍፁም በቤተ ክርስቲያን አላገለገልኩም። በዓለም ውስጥ በጣም ብዙ ጣኦቶች ነበሩኝ፣ እና ያ አበላሸኝ(በከለኝ)። ለዛ ነው እኔ እዚህ ያለሁት። እኔ በዛ ኢጅግ በጣም እጸጸታለሁ፣”* እሷ ጮኸች። ከዛ፣ እሷ ወደጋለው (ሞቃት) ፈሳሽ በተመሳሳይ መልኩ ተወረወረች። እኔ በጣም ፈርቼና አዝኜ ነበር፣ ከዚህ በላይ ሁኔታውን ልወስደው አልቻልኩም ነበር። ፊቴ በእንባዎች ተሸፍኖ ነበር፣ እና የሚቃጠለው ሽታ አተነፋፈሴን አስቸጋሪ አድርጎት ነበር። ኢየሱስ ደግሞ እንባዎቼን ማፍሰስ ቀጠለ። **ጌታ** ለኔ አንድ ጠቃሚ መልእክት ነበረው፣ *“ወደ መንግሥተ ሰማይ አንዴ ብቻ ነው እድል ያላችሁ፣ እናም ያ በስጋዊ አካላችሁ በሕይወት እየኖራችሁ ሳላችሁ ብቻ።”* እኔ ምንም ማድረግ አልቻልኩም ግን ሲሰቃዩ ማየት። በሲኦል ውስጥ ያለው እሳት ከእኛ መሬታዊው(ምድራዊው) ዓለም ውስጥ ካለው እሳት ጋር ሊወዳደር አይችልም።

**ሊ, ዩ-ክዩንግ:**



ከጠዋቱ 1:30(7:30 am) እስኪሆን ድረስ ከጸለይኩ በኋላ፣ የተወሰነ እንቅልፍ ለማግኘት ተስፋ እያደረግሁ እቤት መጣሁ፣ እቤት ውስጥ አንድ መገኘት ተሰማኝ። ዐይኖቼን ገለጥኩ፣ ግን ምንም ነገር አላየሁም። ዐይኖቼን በድጋሜ ስጨፍን፣ ኢየሱስ ከአጠገቤ ተቀምጦ ነበር። አንድ ድንገተኛ ፍርሃት በላዬ ላይ መጣ፣ እና አካሌ በዝይ እብጠቶች ተሸፈነ። በድፍረት በልሳኖች ጸለይኩ። **ኢየሱስ** ነው ብዬ ያሰብኩት ሰው በድንገት ወደ አንድ ጭለማ ሰይጣን ተለወጠ፣ እና ጥቁር ሰማያዊ ዐይኖች ነበሩት። ሰይጣኑ ዐይኖቹን አሽከረከራቸው(ጠቀለላቸው)፣ እና እጆቹን ወደላይ አንስቶ የጌታን ጸሎት ለመጸለይ(ለመድገም) ሞከረ። ከዛ ጮኸ፣ “*አጋንንቶች ሁሉ ተነሱ!*” እኔ ደንግጬ ነበር። በትእዛዝ ጩኸት እኔ እንዲህ አልኩ፣ *“አንተ ጋኔን፣ **በኢየሱስ ስም**፣ ከእኔ ሽሽ።”* ጋኔኑም(ሰይጣኑም) ወዲያውኑ ጠፋ።

# ==== ቀን 10 ====

**<u>ኪም, ጁ-ኢዩን:</u>**

በሙሉ ኃይሌ በልሳኖች እየጸለይኩ እያለሁ፣ ቀይ ድራጎን ከፊቴ መጣ። በፍጥነት እላዬ ላይ ዘለለብኝ። ድራጎኑ የሚያስደነግጥ (የሚያስፈራ) የአዞ ዐይኖች ከወፍራምና ሹል ቀንዳማ ጥፍሮች ጋር ነበሩት፣ እና የሾሉ ቀንዳማ ጥፍሮቹን ወደእኔ በማድረግ(በመጠቆም) ሊያስደነግጠኝ ጣረ። ቀፋፊና የሚያጥወለውል ጭስ ከአፍንጫው ቀዳዳዎች ይወጣ ነበር። *"ሰይጣን፣ አንተ እጅግ አስቀያሚ፣ በ**ኢየሱስ** ስም ከእኔ ሽሽ።"* እንደተናነደደች ሴት እየተቆጣሁ ነበር። ድራጎኑ ከዛ ወደ ወንድም ሀክ-ሱንግ አቀና። ሀክ-ሱንግ በድንገት መደንገጥ ጀመረ። የልሳኖች ጸሎቶቹ በይበልጥ ኃይለኛና ከፍ ያለ(በጣም የሚጮህ) መሆን ጀመረ። እኔ እንዳደረኩት እሱም ጮኸ፣ *"ሰይጣን፣ በ**ኢየሱስ** ስም ከእኔ ሽሽ።"* ከትንሽ ጊዜ በኋላ ድራጎኑ ቀረበኝ፣ እና ወደ ጥቁር ድራጎን ተለወጠ። በክፉ (ሰይጣናዊ) ሳቅ፣ ድራጎኑ ማውራት ጀመረ:- *"አትጸልዪ፣ ለምንድን ነው ስትጸልዪ በጣም ያለምንም ጥረት ዐይኖችሽን የምትከፍቺው? ምክንያቱ ይህ ከሆነ፣ ከዛ ዐይኖችሽን ክፈቺ። ለምንድን ነው በጸሎት ጊዜ የግድ ዐይኖችሽን የምትጨፍኚው? በዚህ ቅጽበት ዐይኖችሽን ክፈቺ። ለምንድን ነው ዛሬ በታላቅ ኃይል እየጸለይሽ ያለሽው?"* በጸሎቶች ያለኝን ትኩረቴን ሊሰብር ሞከረ። በድጋሚ እንዲህ ብዬ ጮህኩኝ፣ *"እጅግ አስቀያሚ ሰይጣን፣ በ**ኢየሱስ** ስም ከእኔ ሽሽ።"* ቢሆንም፣ ድራጎኑ በጣም በቀላሉ አልሄደም። በመሆኑም የ**ኢየሱስ**ን ስም በይበልጥ በጣም በግልጽ መግለጽ ነበረብኝ። በ**ኢየሱስ** ስም በመጮኼ፣ ድራጎኑ አንድ ጊዜ በቁጣ፣ በቀዳዳ ዐይኖቹ እያፈጠጠ፣ ጥርሶቹን እያፋጨ ወደኔ ዞረና ሸሸ።





ከቆይታ በኋላ ሌላ ክፉ መንፈስ በቁጣ አፈጠጠብኝ፣ እና ወደእኔ መንቀሳቀስ ጀመረ። ያ ክፉ መንፈስ በብዙ የኮሪያ ሆነር ፊልሞች ላይ ችና ቴሌቪዠን ላይ የታየ ታዋቂ ሴት ክፉ መንፈስ እንደ ሆነ አስተዋልኩ። እኔ እየፈራሁ መጣሁ፣ ግን ፍርሃትን የምገልጽ ከሆነ፣ እንድታጠቃኝ ሙሉ ልብ (ድፍረት) እንደሚሰጣት አውቅ ነበር። ከመንፈሱ ጋር በጸሎቶች ስዋጋ፣ በሙሉ ጥንካሬዬ፣ ምንም ዓይነት ፍርሃት ላለመግለጽ ጣርኩ። የዚህ አስፈሪ መንፈስ አላማ ሰዎችን በፍርሃት ወደሞት እንዲሄዱ ማድረግ ነው። ከአፏ ጫፎች ደም ይንጠባጠባል፣ እና ጸጉሯ የተመሰቃቀለና ንጹህ ያልሆነ ነው። ቅዱስ ያልሆነ ድምጽና በጣም አስቀያሚ የሆነ ሳቅ አሰማች። በሙሉ ጥንካሬዬ ጮህኩ፣ *"በ**ኢየሱስ** ስም ከእኔ ሽሽ።"* እናም ጠፋ።

ከቆይታ በኋላ ጌታ ኢየሱስ ከፊቴ ተገለጠ። ቢሆንም የተሳሳተ ነገር እንዳለ ተሰማኝ። የማያረጋጋ (የሚያስጨንቅ) ነገር ተሰማኝ፣ እና ጌታን ሳየው ፍርሃት ተሰማኝ። ሰይጣን የብርሃን መልአክ መስሎ ሊገለጥ ስለሚችል፣ አደጋዎችን ለማስወገድ መጠንቀቅ እንዳለብን ፓስተሬ የነገረኝን አስታወስኩ። መናፍስትን መለየት ካልቻልኩ፣ በልሳኖች መጸለይ ወይም **የእግዚአብሔርን ቃል** መጥቀስ እንዳለብኝ ተነግሮኛል። ይህንን **ኢየሱስ** በልሳኖች በመጸለይ ለማረጋገጥ ጣርኩ። በልሳኖች በጸለይኩበት ሰዓት፣ የጌታን ፊት መስሎ የተገለጠው ሌላ መልክ መያዝና ወደ ጥቁር መለወጥ ጀመረ። ሰይጣኑ ኢየሱስን አስመስሎ ወደኔ መጣ። የሰይጣኑ ዐይኖች በሁሉም አቅጣጫዎች ይሽከረከርና እኔን ከጸሎት ለማዘናጋት ሲሞክር ከኔ ርቆ አይሄድም ነበር።




**<u>እህት ቤይክ, ቦንግ-ንዮ:</u>**

ዛሬ በልሳኖች እየጸለይኩ እያለ፣ **ጌታ ኢየሱስ** ወደ እኔ መጣ። እኔም አለቀስኩኝ፣ ***"ጌታ ሆይ፣*** *ጌታ ሆይ።"* **ኢየሱስ** ተናገረና እንዲህ አለ:- ***"ማልቀስ አቁሚ። እኔ የመጣሁት ወደ መንግሥተ ሰማይ ልወስድሽ ነው። ከእኔ ጋር ነይ።"*** **ጌታ** እጄን ሲይዝ ፊቱ ላይ ስለኔ የሀዘን ስሜት ነበር። መንግሥተ ሰማይን በጎበኘሁበት ጊዜ ሁሉ፣ ገደብ በሌላቸውና ዘላለማዊ በሆኑት በሚስጥሮቹ ሁሉ እጅግ እደነቃለሁ። በጣም ጥሩ (ማራኪ) በሆኑት እይታዎች እደነቃለሁ። መንግሥተ ሰማይን ለማየትና ለመለማመድ ዘላለም እንደሚወስድ ተሰማኝ። **ኢየሱስ** ሄጄ በመንግሥተ ሰማይ ያለውን ቤተ ክርስቲያን እንድቃኝ (በትኩረት እንድመለከት) ነገረኝ። እኛ እዛ እንደደረስን፣ እጹብ ድንቅ የሆነውን እጅግ ግዙፍ ሕንፃ ስመለከት በጣም ከመደነቄ የተነሳ መንጋጋዬ ወረደ። ጮህኩኝ፣ *"ዋው!"* እጅግ በታላቅ የደስታና የሐሴት ስሜት ላይ ነበርኩ። እጅግ በጣም ትልቅ ነበር፣ የገነትን ሰማይ መንካት የሚችል ሆኖ ነው የታየው።

ከቆይታ በኋላ፣ መንግሥተ ሰማይን እየጎበኘን እያለ፣ **ኢየሱስ** እንዲህ አለ፡- *"ቦንግ-ንዮ፣ የመንግሥተ ሰማይን ከፍተኛ ጫፍ ለመጎብኘት እንሂድ።"* ጫፉ ላይ ስንድርስ፣ የመንግሥተ ሰማይን የተለያዩ ቦታዎችን ማየት ችዬ ነበር። ብዙ መላእክትን አየሁ፣ ብብዙ የተለያዩ አበባዎች ያሉበት እጅግ በጣም ትልቅ መናፈሻ አየሁ። ያየኋቸውን ሁሉንም የተለያዩ ዓይነት አትክልቶችና አበባዎችን ለመቁጠር ለኔ የማይቻል ነበር። እንደ ክሪስታል ንጹህ የሆነ መጨረሻ የሌለውን ውቅያኖስ ማየት ችዬ ነበር። ውኃው ላይ የሚንሳፈፉ የሚያማምሩ ብዙ መርከቦች ነበሩ።

በኋላ ላይ፣ ወደ ምድር ስመለስ፣ መንግሥተ ሰማይን የጎበኘሁ ቢሆንም እንኳ፣ በሲኦል ያሉትን ቤተሰቦቼንና ወንድሜን በድጋሜ አስታወስኩ። ለብዙ ሰዓታት አለቀስኩ፣ እና ምን ማድረግ እንዳለብኝ አላውቅም። ከትንሽ ቆይታ በኋላ፣ አስራ አምስት መላእክት ያሉት አንድ ማሕበር ወደኔ መጣ (የአንድ ማሕበር አባላት አስራ አምስት መላእክት ወደኔ መጡ)። *"ጌታ ወደ መሬት ሄደን እህት ቤይክ, ቦንግ-ንዮን እንድናጽናናት አዘዘን። ለዛ ነው እኛ እዚህ ያለነው።"* በዙሪያዬ ከበቡኝና በቅንነትና በሚያፅናኑ ቃላት ያገለግሉኝ(ያፅናኑኝ) ጀመር። ከትንሽ ቆይታ በኋላ መረጋጋት ችዬ ነበር፣ እንባዬም ታብሶ ነበር።

ከቆይታ በኋላ፣ መጸለይ ስቀጥል፣ በድንገት ሰማይ ተከፍቶ አየሁ፣ እና **እግዚአብሔር አብ(አባት)** በሰማይ(ሰማያዊ) ዙፋኑ ላይ ተቀምጦ ነበረ። እርሱ ተናገረና ማልቀስ እንዳቆም ነገረኝ። **መንፈስ ቅዱስ** መጣና ለስለስ ባለ ድምጽ እንዲህ አለኝ፡- *"እኔ ለአንቺና ለእህት ካንግ, ህዩን-ጃ የመፈወስ ስጦታና የመንፈስ ቅዱስን እሳት እሰጣችኋለሁ። ቢሆንም፣ እናንተ በቁርጠኝነት(በትጋት) እነሱን(ስጦታዎቹን) መፈለግ አለባችሁ።"* **ኢየሱስ** ከ**አባቱ** ቀጥሎ እንደቆመ፣ እርሱ እንዲህ አለኝ፣ "*ቦንግ-ንዮ፣ በጸሎት ጊዜ ደካማና ጥንካሬ(ኃይል) የሌለሽ ስትሆኝ፣ እኔ በመንፈስ ቅዱስ ኃይል እቀባሻለሁ።*"



ከጥቂት ጊዜ በኋላ፣ **ኢየሱስ** በታላቅ ቆራጥ ድምጽ መናገር ጀመረ፣ ቤተ ክርስቲያኖችና ፓስተሮች በከንቱ እያመለኩት እንደሆነ ኢየሱስ ገለጸ። እነሱ ባህልንና የሰውን ስራዎች ይከተላሉ። አብዛኞቹ መልእክቶች አጭርና በመልእክት ፍሬ አልባ(ባዶ) ናቸው። የአምልኮና የምስጋና ጊዜ ርዝመት ተቀባይነት የሌለው እየሆነ መጥቷል። እነሱ የበለጠ ትኩረታቸው መቼ እንደሚያልቅ(እንደሚፈጸም) ነው። የስብከቱ ጊዜ አጭር ሆኗል። **ኢየሱስ** የእርሱን ጭንቀት እየገለፀ ነበር። ባጠቃላይ አገልግሎቶች በርዝመት አንድ ሰዓት አካባቢ ናቸው። ቢሆንም፣ ብዙ አገልግሎቶች ከአንድ ሰዓት በታች እየሆኑ መጥተዋል። እነሱ ለመጨረስ በጥድፊያ ውስጥ ናቸው። **ኢየሱስ** በሰባኪዎች አካል ውስጥ ለመገለጥ ይፈልጋል። ነገር ግን ፓስተሮች በመንፈስ ሳይሆን በስጋ ነው የሚሰብኩት። እነሱ በመንፈስ ከመስበክ ይልቅ ስለ ሰዓት አመራር (ታይም ማኔኝመንት) ነው የበለጠ የሚያተኩሩት። ባነሰ አምልኮና አገልግሎት ሰዓት፣ ብዙ ፓስተሮች(ካህናት) ትርፍ ሰዓቱን ለግላዊ ጥቅም እያዋሉ ናቸው፣ እንደ መመገብ፣ ከአባላቱ ጋር ጉዞ መሄድ፣ እና በሌሎች ጥቅም በሌላቸው ነገሮች ላይ ጊዜያቸውን እያጠፉ(እያባከኑ) ነው። አንዳንድ ፓስተሮች(ካህናት) በሚስቡ(በማራኪ) እህቶች እየተምታቱና ራሳቸውን እያሞኙ እና ታላቅ ትኩረት ለሴቶቹ ውበት እየሰጡ ናቸው። ከዚህም በላይ፣ አንዳንድ ፓስተሮች አባላቶቻቸውን በእኩል አክብሮት አያስተናግዷቸውም(አያዩዋቸውም)። ሀብታም(ባለጸጋ) አባላት ብር ከሌላቸው አባላት በላይ ብዙ ሰዓትና አክብሮት ይሰጣቸዋል። እንደዚህ አይነት ፓስተሮች ለ**እግዚአብሔር** ክብር በቂ ሰዓት በጸሎት እያሳለፉ አይደለም(እየጸለዩ አይደለም)፣ ነገር ግን ዋጋ ቢስ ጸሎት እየጸለዩ ነው፣ ይህም ለጌታችን የሚያናድድ(የሚያስደነግጥ) እና የሚያስጨንቅ ነው። መልእክቶቹ በ**መንፈስ ቅዱስ** የተመሩ አይደሉም። መልእክቶቹ የሚቀርቡት በፓስተሮቹ(በካህናቱ) የእውቀትና የሥጋ ጥንካሬ ነው። **ከመንፈስ ቅዱስ** ያልሆኑ መልዕክቶች አጭር እና ከንቱ ስብከት በመሆን ይቋጫሉ። ሰባኪያኑ በ**መንፈስ ቅዱስ** ለመመራት ሳይሆን በአባላቱ ፈቃድ ለመመራት ነው የተመረጡት። **ኢየሱስ** ፓስተሮችን(ካህናትን) ለእግዚአብሔር ክብር በሀይል ለመቀባትና ለመጠቀም ይሻል። ነገር ግን፣ ፓስተሮች፣ በራሳቸው ፈቃድ የጌታን ቅባት መፈለግ አቁመዋል(ትተዋል)። አሁን የሥጋ ሀሳባቸው(አእምሮዋቸው) በመንፈሳቸው ላይ ይገዛል። ብዙ ሰባኪያን **የእግዚአብሔርን ልብ**ና መሻቶች መስማት አይችሉም። **እግዚአብሔር** በጥልቀት አዝኗል። ቤተ ክርስቲያን ሲሰፉ ወይም ሰገነባ፣ አንዳንድ ሰባኪያን ለራሳቸው ክብርና ትምክህት(ኩራት) ሲሉ ያደርጉታል። በልባቸው፣ ሕንፃው ለራሳቸው አንድ ታላቅ ቅርስ(ሀውልት) ነው። እንዲህ አይነት ፓስተሮች በጣም ጥቂት ሰዓት በጸሎት ያሳልፋሉ እና በዚህ ዓለም ቁስ አካል ቀዳሚነት በማመን አስቀድመው ተይዘዋል።

**ጌታ** ስለነዚህ ነገሮች እንደነገረኝ፣ በፊቱ ላይ የነበረውን የሀዘን መግለጫ አየሁ። ቢሆንም፣ ብዙ ሰባኪያን በጣም አስደናቂ ስለሆኑት ሕንፃዎቻቸው መመካት ይችላሉ፣ መንግሥተ ሰማይ ያንን እንደ ዋጋ ቢስ ይቆጥረዋል።


የመንግሥተ ሰማይ መንገድ ከመሬት መንገድ ከፍ ያለ ነው። በመሬት አንድ ሰው ጠቃሚ ነው ብሎ የተገነዘበው በመንግሥተ ሰማይ ቀለል ያለ ሊሆን ይችላል። **ኢየሱስ** ይህን ነገረኝ፣ *“ሁሉም ፓስተሮች አይደሉም ክፉ የሆኑት፤ ነገር ግን፣ የማይታዘዙት የግድ ስነ ስርዓት መያዝ አለባቸው። እነሱ ካልተፀፀቱ(ንሰሐ ካልገቡ)፣ እኔ ሲኦል እወረውራቸዋለሁ። በሲኦል እነሱ ይሠቃያሉ፣ እና በአጭር ጊዜ፣ እኔ እዛ እወስድሻለሁ፣ ከእነሱ* (ከማይታዘዙት ከኃጢአተኛ ፓስተሮች) *አስቀድመው እዛ (ሲኦል) የሄዱትን እነዛን (ንሰሐ ሳይገቡ የሞቱ አሁን በሲኦል ያሉ ፓስተሮች) የምትመሰክሪበት።”*

ከቆይታ በኋላ በዛ ቀን፣ አንድ ነገር ለመረዳት ከ**ጌታ** እርዳታ ፈለግሁ። አንዳንድ አማኞች፣ ለአስርት አመታት ያህል ክርስቲያኖች የሆኑ እንደነገሩኝ፣ አንድ ሰው ሲሞት፣ እሱ ወይም እሷ፣ ወይ ወደገነት ወይ ወደ ሲኦል ይገባሉ። አንድ ሰው በምድር እየኖረ እያለ(በምድራዊ ሕይወት እያለ) ገነትን ወይም ሲኦልን መጎብኘት አይችልም ይላሉ። እነሱ ይህ እርባና የለሽ (መጃጃል) ነው ይላሉ። የእኔ ቤተ ክርስቲያን ህግ(ዶክትሪን) እና እምነቶች ነበረው ይሉኛል። እነሱ ስለ ጸሎት ግንኙነታችንና ስለርዝመቱ አሸሙራዊ አስተያየቶችን በማድረግ ይሳለቃሉ። እነሱ በተጨማሪ ፓስተር ኪምና አባላቶቹ ከልት (a cult) ሊሆኑ ይችላሉ ይላሉ። ስለዚህ እኔ ጸለይኩ፣ *“እባክህን **ጌታ** ሆይ፣ ቤተ ክርስቲያናችን የእውን ከልት (a cult) ቢሆንስ? ለቤተሰቤ ምን ይሆናል? (ቤተ ሰቤ ላይ ምን ይሆናል?)”* **ጌታ** እንዲህ አለ፦ *“ከልት ምንድን ነው? ሰዎች በልዩነታቸው፣ በቤተ ክርስቲያን (በሀይማኖት) ክፍላቸው(ዲኖሚኔሽንስ)ና በራሳቸው አስተሳሰብ(ዶክትሪን) እየተካሰሱና እየተፈራረዱ ናቸው። እነሱ ሀጢአት እየፈጸሙ ነው። ነገር ግን እኔ በአንቺ ቤተ ክርስቲያን እጅግ ተደስቻለሁ። አንቺና የቤተ ክርስቲያንሽ አባላት ሌሊቱን ሙሉ ያለ ማቋረጥ ትጸልያላችሁ። እናንተን ያሰቃዩዋችሁ እና ሌ ከልት ብለው የጠሯችሁ እኔ እየኖርኩ እንደሆነ(እየኖርኩ እንዳለሁ)ና እኔ ጌታ እንደሆንኩ ያውቃሉ። አንቺ የታመሙትን የመፈወስ ስጦታ ተቀብለሻል እና አጋንንትን ማስወጣት ትችያለሽ። በተጨማሪ አንቺ መንፈስ ቅዱስን እየተከተልሽ ነው በመኖር ላይ ያለሽው።”* **ኢየሱስ** ቀጠለ፦ *“እርስ በእርሳቸው የሚፈርዱና የሚከሱ ሰዎች አስከፊ(አሰቃቂ) ቅጣት ይቀበላሉ። እነሱ ከእውነቱ መንገድ እንዲያርቁሽ(አርቀው እንዲመሩሽ) አትፍቀጂ። እኔ በጸሎታችሁ እጅግ በጣም ተደስቻለሁ። አትጨነቂ። እኔ አንቺንና ቤተ ክርስቲያንሽን እጠብቃለሁ። በመሆኑም ለሕዝቦቼ ሁሉ ራሴን መግለጥና መንፈሳዊ ስጦታዎችን ለእነሱ መስጠት(እንዲሰጣቸው መፍቀድ) የእኔ ምኞት ነው፣ እነሱ እኔን እየፈለጉኝ አይደለም። ብዙዎች እንደእኔ ፈቃድ እየጸለዩ አይደለም።”* እኔም እርሱን ጠየኩት፣ *“**ኢየሱስ**፣ ቤተ ክርስቲያናችን ምን እየሆነ ይመጣል?”* **ኢየሱስ** አለ፦ *“እናንተ በመንፈስ ቅዱስ ለመሞላት እና በጣም በቶሎ የልሳኖችን(በልሳኖች የመናገር) ስጦታ ለመቀበል መልካም እድል ያገኛችሁ ናችሁ። ቅዱስ እሳቱ በቤተ ክርስቲያኑ አባላት ይሰማና አባላቱ ይቀበሉታል።”*

በረጅም አገልግሎቶች ጊዜ፣ ፓስተር ኪም በመንፈስ ቅዱስ የቅባት ጥንካሬ(ኃይል) ውስጥ በሀይለኛው ይሰብካል። በአገልግሎቱ ጊዜ ከአገልግሎቱ ርዝመት የተነሳ አንዳንድ ሰዎች ወድቀን የምንቀር ሊመስላቸው ይችላል፤ ነገር ግን፣ በኃይል የተሞላው ስብከት፣ ምስጋና፣ ዝማሬና በእሳት የተቀጣጠለ(በመንፈስ ቅዱስ እሳት የተሞላ) አምልኮ ሁሉም የሚደረገው(የሚካሄደው) በጥንካሬ ተሞልተን እጅግ ከፍ ባለ በታላቅ ርህራሄ ነው፣ እና በቀጣዩ ቀን ውስጥ ሌሊቱን ሙሉ ሊካሄድ ይችላል። [በአውሮፓውያን የቀን አቆጣጠር ከሌሊቱ ስድስት ሰዓት በኋላ እንደ ነገ(ቀጣይ ቀን) ስለሚቆጠር ነው]። አንድ ቀን፣ ፓስተራችን ፊቱ ወደ ቀይ እስኪለወጥ ድረስ በሙሉ ልብ (በሀይል) ሰበከ። ሀይለኛና ጥልቅ ስሜት ባለው በስብከቱ ጊዜ፣ የ**እግዚአብሔር**ን ታላቅ ዙፋን ራእይ አየሁ። **እግዚአብሔር አብ(አባት)** የቅብዓት ዘይት ወደታች እያፈሰሰ ነበር። መንፈስ ቅዱስ ፓስተሩን በእሳት እየቀባው ተገለጠ (ታየ)። **እግዚአብሔር አብ** ያለማቋረጥ እሳትና የቅብዓት ዘይት ፓስተሩ ላይ እያፈሰሰ ማየት ችዬ ነበር። ስብከቱ በጣም ሀይለኛና አስደሳች እየሆነ መጣ። ጌታ ኢየሱስ በደስታ እየሳቀ አየሁት። **ጌታ ኢየሱስ** አንድ መልአክን የአገልግሎቱን ሁኔታዎች በትጋት እንዲቀዳ (እንዲመዘግብ) ነገረው። መልአኩ ተቀበለና ታዘዘ። ኢየሱስን በኮሪያ ሳይቀር ብዙ ቅርንጫፎች ስላሉት ስለ ሌላ ዓለም አቀፋዊ ቤተ ክርስቲያን ጠየኩት፣ አንዳንዶች ቁጥራቸው ብዙ የሆነው በታሪካቸውና በባህላቸው ምክንያት ነው ይላሉ። *“እነሱ እንደእኛ አማኞች ናቸው?”* **ኢየሱስን** ጠየቅሁት። **ኢየሱስ**ም መለሰ፦ *“እነሱ በእኔ ካመኑ፣ በእርግጥ እነሱ ይድናሉ። ግን ያ ቤተ ክርስቲያን የእግዚአብሔርን ቃል ከዓለም ጋር በማጋባት ዝቅ አድርጓል።”*

ይህን የተለየ ቤተ ክርስቲያን እየተወያየንበት እያለ፣ በራእይ፣ የአጋንንትን ንጉስ እንዳይ ተደረገ። ይህ ክፉ ጋኔን የተጨነቀ፣ የተደናገጠና በዛ በተለየው ቤተ ክርስቲያን የእቅዱን የፈራ(የሰጋ) መስሎ ታየ። **ኢየሱስ** እንዲህ አለ፦ *“ብዙ የእግዚአብሔር ሕዝብ ሰይጣንንና ክፉ መናፍስቱን ቻልተኞች ናቸው። ሕዝቤ ለጠላት(ለሰይጣን) ብዙ ትኩረት ሳይሰጡ ኑሯቸውን በታማኝነት እየኖሩ ናቸው፤ ነገር ግን፣ ሰይጣን ስራችሁን ለማደናቀፍ ይፈትናል። ጥሩ ጎበዝ ሁኑ።”*

ከዚያ በኋላ፣ ከፓስተሩ ጎን እየጸለይኩ እያለ፣ አንድ በጣም ትልቅ (ግዙፍ) ቀይ ድራጎን ተገለጠ። አውሬው በፊተኛው በር ገባ። የሰማይን ያህል ከፍ ያለ(የሰማይን ያህል ረጅም) ይመስላል። የአውሬው ገጽታ(ሁነታ) ንጹህ ቁጣ (ሙሉ በሙሉ ቁጣ) ነበር። አፍንጫውን ማቁነጥነጥ(ማንቀሳቀስ) ቀጠለ። ድራጎኑ ተናገረ፣ *"እኔ አካልሽ ውስጥ ለመግባት እየሞከርኩ ነው። እንዴት ብትደፍሪኝ ነው እኔን የምትገጥሚኝ! እኔ የሲኦል ንጉስ ነኝ! ሁሉም በሲኦል ያሉ እኔን በፍርሃት ይታዘዙኛል። ማን እንደሆንሽ ታስቢያለሽ? አንቺ ማንም ነሽ። ማንነቴን የመግለጥ ምንም መብት የለሽም። አሃ: አሁን ማን እንደሆንሽ አወኩ። ከበታቾቼ አንዱ በቅርቡ ስላንቺ አስታውቆኛል። ይህን የበታቼን ከዚህ በፊት ብዙ ሰዎችን እንዲያስትና ወደ ሲኦል እንዲመራ ነግሬው ነበር። ነገር ግን፣ እሱ ያለ ስኬት ተመልሶ መጣ። ለምን እንደወደቀ (እንዳልተሳካለት) ስጠይቀው፣ እሱ እንዲህ አለ፣ 'የእኔ ንጉስ፣ ለምን በጣም ከባድ እንደሆነ በራስህ የግድ ማየት አለብህ። እኔ ሰዎችን ራስን ወደማጥፋት በቀላሉ የምመራ መስሎኝ ነበር። ነገር ግን የክርስቲያኖች ጸሎት በጣም ሀይለኛ ነው።' 'ምን እየተናገርክ (እየጠቀስክ) ነው?' እኔ የበታቼን ገሠፅኩት። የበታቼን ጥያቄ ማረጋገጥ ነበረብኝ። ያ እውነት ነበር። እኚህን ጸሎቶች ለመዋጋት የማይቻል ያህል ነበር።"* ቢሆንም ድራጎኑ ፈራና እኛን ገሠፀን፣ **ኢየሱስ** ጠብቆን ስለነበር እኛ ደህና ነበርን። ድራጎኑ በንቀት(ጸያፍ) ተራ ነገር ጮኸና እንዲህ አለ፣ *"እኔ እየተደናቀፍኩ ነበር።"* ከዛ **ኢየሱስ** ለአውሬው መለሰለት፣ ***"አንተ የት ያለህ ይመስልሃል? ባለጌና ቁጡ(ሁከተኛ) አትሁን። ከጌታ ቤተ ክርስቲያን(ከ ዘ ሎርድ'ስ ቸርች) አንድ ሰው ከነካህ፣ ትቀጣለህ፣ እና አባቴ ይመታሃል።"*** አውሬው በጣም ተጨናንቆ (አዝኖ) ነበር፣ እና እሱ በድንገት ተሰወረ። **ኢየሱስ** አለ፣ ***"በሲኦል ያለው ያ ድራጎን የክፉ መናፍስት ንጉስ መስሎ ሊያስትሽ ሞክሯል። የዛ የተለየ አውሬ ይህ የመጀመሪያው መገለጥ ነው። እሱ ትእዛዙን ይፈጽሙለት ዘንድ ብዙ ጊዜ የበታቾቹን ወደ መሬት (ምድር) ልኳል። በትጋትና ያለማቋረጥ ጸልዩ። ሁል ጊዜ ጥንቁቅ ሁኚ፣ እና አትጨነቂ፣ ምክንያቱም ሥላሴ አምላክ ሁል ጊዜ ይጠብቅሻል።"***




**<u>ፓስተር ኪም ዮንግ ዱ:</u>**

ማክሰኞ ነበር፣ እና ውጪው ቀዝቃዛ ነበር፣ ከ15 በታች የሆነ ብርዳማ ቅዝቃዜ። ምንም እንኳ የአየር ሁኔታው እንዲህ ቢሆንም፣ አራቱ አባላቶች ወንጌልን ለመስበክ ወደ ውጭ ወጡ። ግን ይህን ከማድረጋቸው በፊት በትጋት በጸሎትና **በመንፈስ ቅዱስ** ኃይል ራሳቸውን አዘጋጅተዋል። **ጌታ** በቅዱስ እሳት ይቀባቸው ነበር። አራቱ በይበልጥ በስኬታማነት ወንጌልን ለመስበክና የታቀደለትን ውጤት እንዲያመጣ ስለአካሄድ ፕላን ተወያዩ። ያለ ድካም **የጌታን** ሥራ በማድረጋቸው ታላቅ ሽልማት እየጠበቃቸው እንደሆነ አውቀዋል። ሁሉም ዘግይተው ተመለሱ፣ እና በደስታ ተሞልተው ነበር። *"ፓስተር፣ ወንጌልን መስበክ እንዲህ አዝናኝ (ተወዳጅ)ና አስደሳች እንደሆነ በፍፁም ተገንዝበን አናውቅም።"* አሉ።

# ==== ቀን 11 ====

**<u>ኪም, ጁ-ኢዩን:</u>**

በግልጽ ቅንነት (በትኩረት) ስጸልይ፣ አንድ ብሩህ ብርሃን ከፊቴ ታየ፣ ከዛ ብርሃን ፊት ለፊት ኢየሱስ ቆመ። ***"ጁ-ኢዩን፣ እወድሻለሁ። ያለማቋረጥ ጸልዩ፣ በትጋት ጸልዩ፣ በሙሉ ልብሽ ጸልዩ። አታቋርጪ።"*** ሙቀት ተሰማኝ እና **ኢየሱስን** የበለጠ በግልጽ ማየት ቻልኩ። ከዛ **ኢየሱስ** ለምን እጆቼን ወደላይ እንዳነሳ እንደነገረኝ አወቅሁ። እንደዛ ሳደርግ **ኢየሱስን** የበለጠ በግልጽ ማየት ችዬ ነበር። እኔ እንዲህ ነገርኩት፣ *"ዋው፣ **ጌታ** ሆይ፣ አንተን በግልጽ ማየት ችያለሁ። ወድጄዋለሁ፣ **ኢየሱስ**። አመሰግንሃለሁ።"* በጣም ጥሩ ስሜት እየተሰማኝ ነበር፣ ስለዚህ ታላቁን ደስታ ለመካፈል ለተወሰነ ጊዜ መጸለይ አቆምኩ። ከዛ ወዲያው አንድ ክፉ መንፈስ ታየ። ከጨለማ የበለጠ ጥቁር ነበር። ያንን በ**ኢየሱስ** ስም አባረርኩት፣ እና እኔ በልሳኖች መጸለይ ቀጠልኩ።



**<u>ሊ, ዩ-ከዩንግ:</u>**

በልሳኖች እየጸለይኩ እያለ፣ ረጅም ሽፋሽፍት ያለው አንድ ክፉ መንፈስ ታየ። እያለቀሰ ነበር፣ እና ምን ለማለት እንደፈለገ እንዳዳምጥ ለመነኝ። *"በጣም ቀዝቃዛ ነው። በጣም በርዶኛል። ልታሞቂኝ የምትችይበት ማንኛውም መንገድ አለ? እባክሽን?"* እኔም መለስኩ፣ *"አንተ ቆሻሻ ክፉ መንፈስ። በ**ኢየሱስ** ስም ከእኔ ሽሽ።"*

**<u>እህት ቤይከ, ቦንግ-ንዮ:</u>**



ዛሬ፣ **ኢየሱስ** ወደ መንግሥተ ሰማይ ወሰደኝ። አንድ ሰው የመንግሥተ ሰማይን እይታ በሰዋዊ ቃላት ሊገልጽ አይችልም። እኛ ከ**እግዚአብሔር** አብ ዙፋን ፊት ነበርን። **የአብ ኃይል** (ግርማ፣ ሞገስ) እና ክብር በጣም ታላቅ ነበር፣ ጭንቅላቴን ማንሳት አልቻልኩም ነበር። በፊቱ ሰገድኹ። **የአባት(የአብ)** ባህርይ የማይገለጽ(ሊብራራ የማይችል) ነው። የእርሱ ሀይል (ግርማ) ከታላቅነት በላይ ነው። **የአብ**ን ውልብታ (አንዲት ትንሽ ነገር እንኳ) ለማግኘት ጭንቅላቴን ለማንሳት ሞከርኩ። ነገር ግን፣ የብርሃኑ ንፁህ ድምቀት እርሱን ከማየት ከለከለኝ። **እግዚአብሔር አብ** ብርሃን ነው። አንድ ውሱን አእምሮ የእርሱን ክብር ሊረዳውና ሊያስብ አይችልም። **የእግዚአብሔር አብ** ከፍተኛነት (መጠን) የመንግሥተ ሰማይን ከፍታና ጥልቀት የሸፈነ ያህል ነው። ዙፋኑ የመንግሥተ ሰማይን መጨረሻዎች ከምሥራቅ እስከ ምዕራብ የሸፈነ ያህል ነው። ከእርሱ ዙፋን በላይ የደመናዎች ሰልፍ እያንዣበበ ይታያል(ይመስላል)። ከፀሐይ በላይ ደማቅ የሆነ የሚያንፀባርቅ ብርሃን ወደታች ይጎርፋል። ከ**እግዚአብሔር** ፊት ስቆም እንደ አንድ የአቧራ ጠብታ እንደማህል ተሰማኝ።

ከቆይታ በኋላ፣ መንግሥተ ሰማይን እለቀቅሁ እያለ፣ አንድ መልአክ ወደ መሬት ስመለስ አጀበኝ። ነገር ግን ወደ መሬት ተመልሰን እየሄድን እያለ፣ የክፉ መናፍስት ክምችት አሳደዱን። ክፉ መናፍስቱ በጣም አስቀያሚዎችና አስፈሪዎች ነበሩ። ቢሆንም እኔን ያጀበኝ መልአክ በጣም በፍጥነት በረረ፣ ክፉ መናፍስቱም የእሱን ያህል ፈጣን ነበሩ። አንዱ ድራጎን ነበር፣ ሌላው እባብ ነበር፣ ሌላው የእንቁራሪት ጭንቅላት ነበረው፣ እና ሌላው የሰው ጭንቅላት ነበረው። ሲያሳድዱን እየሳቁ ነበር። ለመልአኩ እንዲህ አልኩት፣ *"ከዚህ በላይ በፍጥነት መሄድ እንችላለን?"* ክፉ መናፍስቱ ቀድመውን ከፊታችን ነበሩ እና ወደ ቤተ ክርስቲያን የሚወስደውን መንገድ እየዘጉ ነበር። ሌሎች ክፉ መናፍስት ከኋላችን ነበሩ እና ሊያጠቁን ተዘጋጁ። መልአኩ ጮኸ፣ ***"ጌታ ሆይ፣ እባክህን አሁን ና።"*** መልአኩ እንደጮኸ፣ **ጌታ** ከፊታችን ታየ። እርሱ በታላቅና በኃይለኛ ድምጽ ክፉ መናፍስቱን ገሠጻቸው። ***"እንዴት ብትደፍሩ ነው የእኔን ልጅ ለማጥቃት የምከራችሁት፣ ሂዱ፣ አሁን!"*** በአንድ ሰከንድ ውስጥ ክፉ መናፍስቱ ጠፉ።

# ==== ቀን 12 ====

**<u>እህት ቤይከ, ቦንግ-ንዮ:</u>**



በልሳኖች እየጸለይኩኝ ነበር፣ እና ጸሎት ውስጥ በገባሁ በሰላሳ ደቂቃዎች አምስት መላእክት ወደእኔ ሲበሩ አየሁ። እነሱ ክፉ መናፍስት ያልሆኑና መላእክት መሆናቸውን ለማወቅ መላእክቱን ለመፈተን ወሰንኩ። እኔ በልሳኖች መጸለይ ቀጠልኩ። ፊታቸው ላይ ወዳጃዊ ፈገግታዎችን አየሁ። በትጋት በልሳኖች መጸለይ ስቀጥል መላእክቱ ራሳቸውን ጓደኞች አድርገው አቀረቡ። የትጋት ጸሎቴ መላእክቱን እንደ ጓደኞች ያረጋግጥልኛል ብዬ ገመትኩ። ነገር ግን፣ በአጭር ጊዜ ውስጥ፣ ነጩ ልብሳቸው ወደ ጥቁር ተለወጠ እና መልአካዊ ክንፋቸው ጠፋ። እነሱ ሲንቀሳቀሱ፣ አካላቸው ይርመሰመስና ይጠማዘዝ ነበር። በሙሉ ሀይል በልሳኖች መጸለይ ቀጠልኩ፣ እና እነሱ መሬት ላይ መውደቅ ጀመሩ። በእውነት (ከልብ)፣ በልሳኖች የመጸለይ መንፈሳዊ ስጦታ ሀይለኛና ታላቅ ነው። በአጭር ጊዜ ውስጥ፣ በፊልሞች ያየኋቸውን ጭራቆች መሰሉ። ብዙ አሰቃቂ የሚመስሉ ፍጡራን ነበሩ፣ በጣም የሚያስደነግጡ። **በኢየሱስ ክርስቶስ ስም** ሁሉንም አንድ በአንድ አስወጣኋቸሁ። ሁሉም ሸሹ። ክፉ መናፍስቱን እንዳስወጣኋቸው፣ አንድ **ኢየሱስ** መጣና እንዲህ አለ፣ *"ቦንግ-ንዮ፣ እኔ ጌታሽ ነኝ፣ እመኚኝ!"* ነገር ግን፣ የእሱ ድምጹ አስፈሪ እና ባህሪው ግራ የሆነ ነበር። ምን ጊዜም **ኢየሱስ** ከዚህ በፊት ሲመጣ፣ ረጋ ያለ፣ ዝምተኛና ሰላማዊ ነበር። አሁን ግን ተሸብሬና ፈርቼ ነበር። በራሴ ላይ ያሉት ጸጉሮች ወደላይ መነሳት የጀመሩ መስሎ ተሰማኝ። በሙሉ ልብ፣ ጮህኩ፣ *"በኢየሱስ ስም፣ ከእኔ ሽሽ።"* ወደ አንድ እንግዳ አሰቃቂ እንስሳ ተለወጠ። እኔን አጠቃኝ፣ ነገር ግን፣ በብዙ ጩኸቶች ሸሸ።



ከዛ ሌላ መንፈስ ታየ። በጣም ሳቢ ነበር። *"እንዴት እንዲህ አይነት ሴት በጣም ቆንጆ መምሰል ትችላለች።"* ብዬ አሰብኩ። ክፉ መንፈሱ በዓለም ላይ ካለች ከማንኛዋም ሴት በላይ ቆንጆ ነበር። ከውብ እይታ ጋር ሸንቃጣ፣ አንድ ባለ ሁለት ክፍል የቢዝነስ ሱፍ ለብሳ ነበር። እሷ እኔን ሰላም ለማለት አጎነበሰችና እንዲህ አለች፣ "*ዘ ሎርድ'ስ ቸርችን (የጌታን ቤተ ክርስቲያን) መካፈል ከጀመርሽ (እየተካፈልሽ) ምን ያህል ጊዜ ሆነሽ?*" ጥያቄውን ችላ አልኩትና በልሳኖች መጸለይ ቀጠልኩ። እሷ ከጎኔ ተንበረከከች፣ እና በጣም ያሸበረቀች (ቬሪ elegant) እና ውብ ሆና ታየች፣ አካሌ እብጠት ነበረው። ከትንሽ ቆይታ በኋላ ፊቷ ለሁለት ተከፈለ፣ እና እሷ ወደ አስከፊ (አሰቃቂ) ቅዠት ተለወጠች። ክፉ መንፈሱ ጮኸ፣ "*ቀጥዪና ጸልዪ፣ ነገር ግን ቀላል አይሆንም። እኔ ወደኋላ አላፈገፍግም (አልሸሽም)።*" ክፉ መንፈሱ አልሄደም። **ጌታ** እንዲህ ሲል ሰማሁ:- "***ቦንግ-ንዮ፣ መጸለይ አታቋርጪ። በቀናኢነት ጸልዪ። እኔ ክፉ መንፈሱን እገስፀውና አስታጉለዋለሁ።***" በድንገት ክፉ መንፈሱ ወደ ላይ ወደ አየር ውስጥ በረረ እና ተመልሶ ወደ ውብ ሴት ተለወጠ። በዚህ ጊዜ እሷ የሚያምር የሠርግ ልብስ ለብሳ ነበር። በጣም ቆንጆ(ማራኪ) ትመስላለች። ሴቷ ትልልቅ ክብ ዓይኖቿን እያርገበገበች፣ ወደታች ወደእኔ በረረች። **ጌታ** ጆሮዎቼ ውስጥ ለስለስ ባለ ድምጽ አንሾካሾከና እንዲህ አለ:- "***መጸለይ ቀጥይና እንዴት ውቧ ሴት ወደ አንድ አስቀያሚ መንፈስ ተመልሳ እንደምትለወጥ ተከታተዪ።***" **ጌታ** እንዳዘዘ በቀናኢነት መጸለይ ቀጠልኩ። ከትንሽ ቆይታ በኋላ፣ ተመልሶ ወደ አስቀያሚ መንፈስ ተለወጠ፣ እና በአንድ ተግሳፅ ሸሸ።

በኋላ ላይ፣ **ኢየሱስ** የቀይ ብርሃን አውራጃ (ዘ ሬድ ላይት ዲስትሪክት) በመባል የሚታወቅ አንድ ቦታ በሲኦል ውስጥ አሳየኝ። በአካላት የተሸፈነ አንድ ግዙፍ ተራራ አየሁኝ። የሰዎቹ አካል በትናንሽ ነጭ ትሎች ተሸፍኗል፣ እና እጆቻቸው ታስረው ነበር። ሰዎቹ ግን ትሎቹን ለማስወገድ ምንም ጥረት አያደርጉም። እኚህ ትሎች የሰዎቹን ቆዳ፣ አፍንጫዎች፣ አፍና ጆሮዎች እየበሱ ዘልቀው እየገቡ ነበር። ትሎቹ አካሎቻቸውን ስለበሉባቸው፣ ከጥቂት ቆይታ በኋላ ሰዎቹ ወደ አስቀያሚ አምሳያዎች፣ እና ከዛ ወደ አጽሞች ተለወጡ። እነሱ ሊነገር በማይቻል ህመም ላይ ነበሩ። እኔም እንዲህ አልኩ፣ *"**ጌታ** ሆይ፣ እነዚህ ሰዎች ለምንድን ነው በዚህ ጨካኝ የሥቃይ ቅጣት ውስጥ ያሉት?"* **ኢየሱስ** እንዲህ አለ:- "***በዚህ ቦታ ያሉ ሴቶች አካላቸውን የሸጡ ናቸው። ወንዶቹ ከእነዚህ ሴቶች ጋር ዝሙት የፈጸሙ ናቸው።***" በጣም ሞቃት ነበረ፣ እና እኔ ቦታውን ለመልቀቅ እየፈለግሁ፣ በታላቅ ስቃይ ነበርኩ።

**<u>ኪም, ጁ-ኢዩን:</u>**

ዛሬ ከአጋንንት፣ ከክፉ መናፍስትና ከድራጎኖች ብዙ ጥቃቶች ነበሩ፣ ነገር ግን **በኢየሱስ ኃይል** እያንዳንዱ ሸሹ። ከዛ አካላት የሌላቸው የመናፍስት ቡድን መጣ፣ በእርግጥ እንግዳ በሚመስል ሁኔታ ሁሉም እንደ ዓይን ተቀርፀዋል። እነሱ መጮህ ቀጠሉ፣ "*አትጸልዪ! እኛ ልናምታታሽ ነው።*" እነሱ ደግመው ደጋግመው ይህን ተናገሩት። ፈርቼ እንዳለ፣ እኔ ጮህኩ፣ "በ**ኢየሱስ** ስም፣ ከእኔ ሽሹ።" ግን እነሱ አልሄዱም ነበር፣ እና እነሱ መጥፎ ጫጫታ ማድረግ (ማሰማት) ጀመሩ። ከትንሽ ቆይታ በኋላ **ኢየሱስ** ተመለሰና እንዲህ አለ፣ "***ጁ-ኢዩን፣ ከእኔ በቀር ወደ ማንኛውም ነገር አትመልከቺ ወይም አታዳምጪ።***" እርሱ ጆሮዎቼን በእጆቹ ሸፈነና እንዲህ አለ፣ "***ጁ-ኢዩን፣ ከእኔ ጋር መነጋገር ትችያለሽ።***" በእርሱ መገኘት ክፉ መናፍስቱ ተበታተኑ።

# ==== ቀን 13 ====

**<u>ኪም, ጁ-ኢዩን:</u>**

ዛሬ ከክፉ መናፍስት ሙሉ ጥቃት ነበር። እየጸለይኩ እያለ፣ ሲኦል እንደሆነ ወደ ማውቀው ጨለማ ቦታ ተጓጓዝኩ። አንድ ግዙፍ ክፉ ፍጡርን ዙሪያውን የከበቡ ብዙ ክፉ መናፍስትን አየሁ። ይህ ግዙፍ ፍጡር የሚያሸብርና አስጨናቂ ይመስላል። ይጮህና በሁሉም አቅጣጫዎች ወዲህ ወዲያ ይላል፣ የተደናገረና እረፍት የሌለው መስሎ ታየ። ይህ ግዙፍ ፍጡር፣ በቁጥር የማይቆጠሩትን የሌሎቹ ክፉ መናፍስት መሪ ሆኖ ታየ። እነዛ መናፍስት ከግዙፉ ፍጡር ትእዛዝ እየጠበቁ ነበር። አንድ ትእዛዝ ከተሰጠ በኋላ፣ የማይቆጠሩ ክፉ መናፍስት ወደ አየር ውስጥ በረሩና በእኛ ቤተ ክርስቲያን ታዩ። ፍጥነታቸው ቅጽበታዊ ነው፣ ከአንድ ሰከንድ በታች። ሁሉም ክፉ መናፍስት የአምስት ዓመቷን ሚናን ጨምሮ ሁሉንም የቤተ ክርስቲያኑን አባላት አጠቁ። ነገር ግን፣ በጸሎት ቋንቋዋ፣ "**ባባያ**፣" ብላ በጥብቅ ስትጮህ፣ ከአጠገቧ የነበሩ ክፉ መናፍስት ወደ ኋላ ወደቁ። ጥቃቱ በልሳኖች እየጸለይን በነበርነው ላይ ሁሉም በአንድ ጊዜ ነበር። ክፉ መናፍስቱ ሁሉም አንድ በአንድ ወደቁ። አንድ ጋኔን በጩኸት አንድ ትእዛዝ አስተላለፈ፣ "*ሁላችሁም፣ አዳምጡ። ፓስተር ኪምን አጥቁ። መሪው ከወደቀ፣ ቀሪዎቹ በቀላሉ ይወድቃሉ። እናንተ ደደቦች፣ ምን እየጠበቃችሁ ነው? በሙሉ ሀይል ፓስተር ኪምን አጥቁ።*"

ወዲያውኑ፣ ብዙ ክፉ መናፍስት ታዩና ፓስተር ኪምን አጠቁ። ግን ቀጥሎ የሆነው ነገር በጣም አስደናቂ ነበር፤ እነዚህ አጥቂ ክፉዎቹ መናፈስት ወዲያውኑ ወደቁ። ክፉ መናፍስቱ ተጎድተውና ተሸንፈው ነበር። በጣም በፍጥነት ከሆነው ነገር የተነሳ ሁሉም ፈርተው ነበር። አንዴ በድጋሜ፣ ክፉ ሀይሉ ለማጥቃት ሞከረ፣ ነገር ግን እነሱ በሁሉም አቅጣጫዎች ተሸነፉ። ጥቃቶቹ ቀጠሉ፣ ነገር ግን ውጤቱ አንድ አይነት በመሆን ይፈፀማል። ፓስተሩን መንካት አልቻሉም። እነዛ ክፉ መናፍስት ጥቃቶቻቸው ጥቅም የለሽ መሆኑን ሲገነዘቡ፣ ሁሉም እሱን መፍራትና መሸሽ ጀመሩ። እነሱ በዙሪያው ብቻ ያንዣብባሉ እና ወደ ፓስተሩ ለመቅረብ አይደፍሩም። ፓስተሩን ስመለከተው፣ እሱ ምን ተከስቶ እንደነበር እንኳ አላወቀም ነበር። እሱ በጉልበቶቹ ተንበርክኮና እጆቹን ወደላይ አንስቶ ልብ በሚነካ ሁኔታ ከፍ ባለ ሀይለኛ ድምጽ በጥልቀት በልሳኖች እየጸለየ ነበር። ክፉ መናፍስቱ በፓስተሩ ዙሪያ ሲያንዣብቡ፣ እሱ በሚንጎደጎድ ድምጽ በልሳኖች ይጸልያል። ከዛ አስፈሪዎቹ ክፉ መናፍስት ወደ ግድግዳው ይወረወሩና ወደ ቁርጥራጮች ይሰባበራሉ። ሁሉም በመሸበር ያለቅሳሉ። ክፉ መናፍስቱ እየሸሹ ሳያቸው፣ ጦርነትን እንዳሸነፍኩ ይሰማኛል እና በአሸናፊነት እስቃለሁ። ከዛ ሰይጣኑ በቁጣ ሲጮህ አየሁት፣ *"ፓስተር ኪም አትጸልይ። እንደዚህ እንድታመልጥ የምንፈቅድልህ ይመስልሃል? እኔ እገልሃለሁ፣ ምያለሁ።"* ከዛ ጥርሱን እንገጫገጨና አጋንንቱ ላይ ጮኸባቸው፣ *"እናንተ ደደቦች፣ በሙሉ ጥንካሬያችሁ አንድ ፓስተር እንኳ መያዝ (መቆጣጠር) አትችሉም? ፍጠኑና አጥቁ!"* ከዛ ሰይጣኑ ጮኸ፣ *"አህ፣ ያ ፓስተር እጅግ በጣም የራስምታት ነው። አህህ፣ እንደማብድ አስባለሁ። በቃ ፓስተር ኪምን ብቻውን ተዉት እና አባላቶቹን እናጥቃ። ፍጠኑ።"* መናፍስቱ የቤተ ክርስቲያኑን አባላት ማጥቃት ጀመሩ፣ ነገር ግን አባላቶቹን ሲያጠቁ፣ በሙሉ ሀይል አያጠቋቸውም። በሙሉ ሀይል ሳይሆን፣ በአንድ ሰው (በሰው) ጥቂት ክፉ መናፍስት ብቻ በመሆን አጠቁ። ክፉ መናፍስቶቹ በሁሉም አቅጣጫዎች ተሰራጩ እና በዚህ ጊዜ በቤተ ክርስቲያን ውስጥ ያሉትን እያንዳንዱን ሰው ለማጥቃት ወሰኑ። ሁሉም አይነት ክፉ መናፍስት ነበሩ፣ ሁሉም በተለያዩ አይነትና ቅርፆች መጡ። ሁሉንም ለማብራራት የማይቻል ነው። ነገር ግን፣ ምንም ያህል በትልቅ ሀይል ቢያጠቁም፣ ክፉ መናፍስቱ ስኬታማ ለመሆን አልቻሉም። የአባላቱ በልሳኖች ጸሎት፣ ክፉ መናፍስቱን ለማሸሽ (ለመመለስ) ጥንካሬና ኃይል አስገኘ። እነሱ ሲያጠቁ፣ እነሱ ደግሞ ወደኋላ ወደቁ። የክፉ መናፍስቶቹ ንጉስ ጮኸ፣ *"የጌታ ቤተ ክርስቲያን ሰዎች፣ መጸለይ አቁሙ። ለምንድን ነው ለመጸለይ የምትቀጥሉት? ክፉ መናፍስት፣ ምን እያደረጋችሁ ነው? ማንም እነሱን ሊያስቆማቸው አይችልም?"* ሁሉም ክፉ መናፍስት በከፍተኛ ጩኸት (ሁከት) ሮጡ። እዛ የነበሩት ይክፉ መናፍስቱ ብዛት ምንም ለውጥ አላመጣም፣ ምክንያቱም በጀግና(በደፋር) የቤተክርስቲያኑ አባላት የተጸለዩት ጸሎቶች ሁሉንም ክፉ መናፍስት አሸንፏቸዋል።



በኋላ ላይ በዛ ምሽት፣ ሌላ ክፉ መንፈስ ሊያጠቃኝ ሞከረ። እንዲህ አለ፣ *"መጸለይ አቁሚ። መጸለይ እንዳትችዪ አምታታሽና ረብሻሻለሁ። በህመም እረግምሻለሁ። ሃ ሃ ሃ ሃ?"* በክፉ አሳሳቅ ሳቀ። ግን የኢየሱስን ስም በመጠቀም፣ ያ ክፉ መንፈስ ተሸንፏል። ከዛ በኋላ በዛ ምሽት እንኳ፣ በልሳኖች ለመጸለይ እንደቀጠልኩ፣ ወደታች ወደ ሲኦል ተወሰድኩኝ። አንዳንድ ሰይጣኖች ወደ ባለአራት ማእዘን ሳጥኖች አንድ ረጅም ሹል ጦር በመውጋት በግድ እያስገቡ ያሉበት አንድ ቦታ ነበርኩ። በሚበክል ቀንቋ፣ ክፉ መንፈሱ ጮኸ:- *"ፓስተር ነኝ ብለህ ታስባለህ(ታስቢያለሽ)? ምን አይነት ሕይወት ነው የኖርከው(የኖርሺው)? አንተ(አንቺ) ከእኔ ጋር እዚህ በመሆንህ(በመሆንሽ) ፈንድቄአለሁ።"* ክፉ መንፈሱ ሲረግማቸው ሳጥኖቹን በመውጋት ጦሩን ማስገባት ቀጠለ። ከፍ ያሉ፣ ህመም የተሞላባቸው ጩኸቶች ከሳጥኖቹ ውስጥ ወጡ፣ ደምም እየፈሰሰ ይወጣ ነበር።

የሳጥኖቹ የላይኛው ክፍል በሸራ መሸፈናቸውን አስተዋልኩ፣ በላያቸው ላይ ትልቅ መስቀል እንደ ተሰራ ሆኖ ነበር። ሳጥኖቹ ሥርአቱን በጠበቀ ፋሽን ተርታ ይዘው ነበር፣ እና መጨረሻ ሳይኖራቸው ተዘርግተው ነበር። የት እንደሚያልቁ(መጨረሻቸው የት እንደሆነ) ማየት አልቻልኩም። ሳጥኖቹ የሬሳ ሳጥኖች እንደሆኑ ተገነዘብኩ። ክፉ መናፍስቶቹ ያለምህረት ረጅምና ሹል ጦሮቻቸውን በቀዳዳዎቹ በኩል በግድ ያስገቡ ነበር። እኔም **ጌታ**ን ጠየኩት፣ *"**ኢየሱስ**፣ ለምንድን ነው የቀድሞ ፓስተሮች የሬሳ ሳጥኖች እዚህ ያለው?"* **ኢየሱስ** መለሰ:- ***"እኚህ ፓስተሮች (ካህናት) ወንጌሌን አልሰበኩም። እነሱ ሌላ ወንጌል ነው የሰበኩት፣ እና የተከተሏቸው ነውረኛ (የተበላሸ ሥነምግባረ ያላቸው) እየሆኑ መጡ። ይህ የእነሱ የመጨረሻ ውጤት ነው፣ በሲኦል ያለ ቦታ።"*** **ኢየሱስ** እንዲህ አለ:- ***"ነውረኛ ፓስተሮች(ካህናት) የበለጠ ይፈረድባቸዋል።"*** [እዛ ሲኦል ያሉት ፓስተሮች (ካህናት)፣ **የእግዚአብሔርን ቃል** ያላከበሩት፣ በቅድስና እንደ **ጌታ ኢየሱስ ክርስቶስ ቃል** ያልኖሩት፣ ኃጢአት ቢሠሩ ንስሐ ያልገቡ፣ እንደ **እግዚአብሔር ፈቃድ** ያልኖሩት፣ **መንፈስ ቅዱስን**

የተሳደቡና፣ ለሰዎች ንፅህና ቅድስና፣ **ለእግዚአብሔር ኢየሱስ ክርስቶስ** ታዛዥ መሆንን ያላስተማሩ፣ ጽድቅ፣ ንስሐ፣ ንጹህ ልቡና ቅድስና እንዲኖራቸው፣ **ጌታ ኢየሱስ ክርስቶስ**ን በሙሉ ልባቸው ነፍሳቸው ኃይላቸው እንዲከተሉ ያላስተማሩ ናቸው እንጂ በቅድስና የኢየሱስ ክርስቶስን ቃል እየፈጸሙ **የእግዚአብሔር አብን ፈቃድ** ያደረጉትን ፓስተሮች (ካህናት) አይደለም፣ **ጌታ ኢየሱስ ክርስቶስ** እንደተናገረው፡፡]



በሌላኛው የሲኦል ክፍል ውስጥ፣ በሥቃይ ውስጥ ያሉ ሌሎች ሰዎች አየሁ፣ እነሱ እየነደደ ባለ አንድ ትልቅ መጥበሻ ውስጥ ነበሩ፣ *"በጣም ይሞቃል፣ አህህ፣ እርዱ፣ እርዳታ!"* እያሉ ይጮኻሉ፡፡ ትልቁ መጥበሻ ቀይ እያበራ ነበር፣ እና ዘይቱ አካላቸውን ሲነካቸው፣ ሥጋቸው ይፈራርስና አጥንቶቻቸው ብቻ ይቀራሉ፡፡ በተመሰቃቀለ ሁኔታ ዙሪያውን መዝለል ቀጠሉ፡፡ ከዛ ሥጋቸው ይመለስ ነበር፣ ከዛ ሙሉው ዑደት እንደገና ይጀምራል፣ ፍጻሜም የለውም (ይህ ዑደት መጨረሻ የለውም)፡፡ **ኢየሱስ**ን ምን እንዳደረጉ ጠየቅሁት፡፡ **ኢየሱስ** እንዲህ አለ፣ ***"በምድር(በመሬት) ሳሉ፣ ከባለቤቶቻቸው ውጪ በመሄድ ከሌላ ሰው ጋር ዝሙት ይፈጽሙ ነበር፡፡ እነሱ ሥራቸውን በድብቅ ይፈጽሙ ነበር፡፡ እና ለሀጢአታቸው፣ እነሱ በስቃይ ውስጥ ናቸው፡፡"***

ከቆይታ በኋላ፣ **ኢየሱስ** በሲኦል አንድ በጣም ትልቅ ጉድጓድ የነበረበት(ያለበት) አንድ የተለየ ቦታ አሳየኝ፡፡ ገደሉ በሰዎች ተሞልቷል፡፡ ብዙዎች(ብዙ ሰዎች) በእሳት እየጋዩ ነበር፡፡ በራሱ ሕይወት ያለው የሚመስል ቀይ-በጣም ሞቃት እሳት ታየ፡፡ ከኃይለኛው ሙቀት (ግለት) የተነሳ እየጮኹ፣ ጉድጓዱ ውስጥ ሰዎች እየሮጡ ነበረ፡፡ **ኢየሱስ** አብራራ፡- ***"እነዚህ በተሳሳተ(በውሸት) ሃይማኖት ያመኑ ወይም ወንጌልን ሳይቀበሉ የቀሩ (የጣሉ) ሰዎች ናቸው፡፡"***

# ==== ቀን 14 ====

**ኪም, ጁ-ኢዩን:**

በኃይል ልብ በሚነካ ሁኔታ እየጸለይኩ ነበር፣ እና ከጥቂት ጊዜ በኋላ አንድ ክፉ መንፈስ ነጭ ልብስ የለበሰች ወጣት ሴት መስሎ አስጠሊታ ሆኖ ታየ፡፡ ከአፏ የሚንጠባጠብ ደም ነበራት፡፡ *"አትጸልዪ፡፡ እኔ ላሸንፍሽ ነው፡፡"* እኔም መለስኩ፣ *"አንተ ቆሻሻ ክፉ መንፈስ፣ በ**ኢየሱስ** ስም፣ ከእኔ ሽሽ፣"* እና እሷ ሸሸች፡፡

ከዛ አንድ በጣም ቁጡ ቀይ ድራጎን ቀረበኝ፣ እና ሌላ ብዙ ክፉ መናፍስት መታየት ጀመሩ፡፡ በኃይል ልብ በሚነካ ሁኔታ በይበልጥ ስጸልይ፣ ጠንካራ ክፉ መናፍስት እየተገለጡ እንደሆነ ተሰማኝ፡፡ በተለየ ሁኔታ፣ በዚህ ጊዜ፣ መንፈሴ ወደ መንግሥተ ሰማይ እየቀረበች እንደሆነ ተሰማኝ፡፡ ክፉ መናፍስቱ መንግሥተ ሰማይ እንዳልገባ እያስፈራሩኝ ሊያግዱኝ እየሞከሩ ነበር፡፡ ስለዚህ እኔ ዓይኖቼ ተጨፍነው በቀናኢነት በልሳኖች ጸለይኩ፡፡ ሁሉንም ለማስወጣት ሞከርኩ፣ ነገር ግን ቀይ ፊት ድራጎኑ ተቋቋመ፡፡ በስተመጨረሻ እስኪሸሽ ድረስ በቀጣይነት እሱን መገሰጽ አስፈልጎኝ ነበር፡፡

**ጌታ** መጣ፣ እና እሱ በእኔ በጣም የተደነቀ (የተገረመ) ይመስል ነበር፣ እንደ ራሴ አይነት አንድ ወጣት ክፉ መናፍስቱን ስታስወጣ፡፡ **ኢየሱስ** በቅጽል ስሜ እና በእውነተኛው ስሜ ጠራኝ፣ ***"ጁ-ኢዩን፣ ጠቃጠቆ፣ በአስደናቂ ሁኔታ እምነትሽ ጨምሯል፣ ስለዚህ ዓይኖችሽ ተጨፍነው በቀናኢነት መጸለይ ቀጥዪ፡፡"***

ስጸልይ ትኩረት አደረግሁ እና በድንገት ጨለማ ሲበዛብኝ ተሰማኝ፣ የቀዘቀዘ ለስላሳ ነፋስ በእኔ ላይ እየነፈሰ ነበር፡፡ ከርቀት አንድ የተከፈተ በር አየሁ፡፡ በድንገት አንድ ደማቅ ብርሃን ታየ፡፡ ዘልቆ እየገባ ያለው ብርሃን እየጠነከረ ሲመጣ ዓይኖቼን ልከፍት ደርሼ ነበር፣ ነገር ግን ዓይኖቼን መክፈት እንዳልቻልኩ ተገነዘብኩ፡፡ ፍርሃት ይበዛብኝ ጀመር እና ከዛ **ኢየሱስ** ታየ፡፡ እርሱ ማብራራት ጀመረ፡- ***"ጁ-ኢዩን፣ በልሳኖች እየጸለይሽ እያለ፣ መንፈስሽ በመላእክት ታጅባ ወደ መንግሥተ ሰማይ እየቀረበች ነበረ፡፡ ነገር ግን ክፉ መናፍስቱ ዓይኖችሽን እንድትገልጪ ሊያስፈራሩሽ ታዩ፡፡ እኔ ግን ጣልቃ ገባሁና ክፉ መናፍስቱ እንዲሸሹ አዘዝኳቸው፡፡ ዓይኖችሽን እንዳትከፍቺ የተከላከልኩት እኔ ነበርኩ፡፡ ጁ-ኢዩን፣ ጥቂት ተጨማሪ መጸለይ እንደሚያስፈልግሽ አስባለሁ፡፡ ዛሬ ወደ መንግሥተ ሰማይ ትሄጃለሽ ብዬ አላስብም፡፡"*** እኔ በጣም ቅር ተሰኘሁ፡፡ **ኢየሱስ** ከዛ በሚያበረታቱ ቃላቶች አጽናናኝ፣ ***"ጁ-ኢዩን፣ አትጨነቂ፣ ወደ መንግሥተ ሰማይ ወስጄሽ ዙሪያውን ላሳይሽ እኔ ቃል እገባልሻለሁ፡፡"***

**ሊ, ሀክ-ሱንግ:**

**ኢየሱስ** ጎበኘኝና ሲኦልን ያሳየኝ ጀመረ። በሲኦል፣ አንድ ትልቅ ክፉ ፍጡር ወንበር ላይ ወደተቀመጠበት ቦታ መጣሁ። ሁኔታውና ውጫዊ ባህሪው እንደሚገልፀው(እንደሚያቀርበው) በዚህ ግዛት ላይ ንጉሥ እንደሆነ ነው። ከፍጡሩ ፊት ለፊት አንድ ትልቅ መሹለኪያ በር መሬቱ ላይ ይገኝ ነበር። ሰዎች ከመሹለኪያው በር ላይ ቆመው ነበር። ይህ ፍጥረት በከባድ ሁኔታ እግሩን ሲያንጓጓ፣ የመሹለኪያው በር ይከፈታል፣ የእሳተ ገሞራ ቅልጥ ድንጋይ ውስጥ ሰዎቹን ይጥላቸዋል። ሰዎቹ የፈላው የእሳተ ገሞራ ቅልጥ ድንጋይ ውስጥ እንደወደቁ፣ እነሱ ወዲያውኑ እሳት ይይዙና በህመም ይጮሃሉ። ስለእነዚህ ሰዎች **ኢየሱስ**ን ጠየኩት እና **ኢየሱስ** መለሰ:- *"እኚህ ሰዎች ኮከብ ቆጣሪዎች፣ የኮከብ ቆጣሪዎች ደንበኞች፣ አስማተኞች፣ ጠንቋዮች፣ እና ራስ ማጥፋትን ፈፅመው የነበሩ ሰዎች(ራሳቸውን ያጠፉ ሰዎች) ነበሩ።"*



**ጌታ** ራሳቸውን ስላጠፉ ሰዎች ሲናገር፣ አጎቴ፣ ከልክ በላይ የሆኑ መድሃኒቶችን በመውሰድ ራስ ማጥፋትን የፈፀመ፣ ወደ እይታዬ ውስጥ መጣ። እሱ ወደ መሹለኪያው በር ተስቦ እና እንዲቆም ተደርጎ ነበር። ፍጡሩ የመሹለኪያ በሩን ለማንጓጓትና ለመልቀቅ እግሩን ወደላይ አነሳ። **ጌታ**ን ለምህረት ለመንኩት፣ *"እባክህን፣ **ኢየሱስ**፣ አጎቴ ወደ እሳተ ገሞራ ቅልጥ ድንጋይ ውስጥ የመውደቅ አደጋ ላይ ነው። እናክህን እርዳው! **ጌታ** ሆይ፣ አጎቴ ሁልጊዜ ለኔ ጥሩ(ደግ) ነበር። አጎቴ፣ በፍጥነት ወደእኔ ጎን ና።"* በሚያሳዝን አስተያየት፣ **ኢየሱስ** እንዲህ አለ:- *"ሀክ-ሱንግ፣ በጣም ዘግይቷል። ሊደረግ የሚችል ምንም ነገር የለም።"* ከጥቂት ቆይታ በኋላ ፍጡሩ እግሩን አንጓጓ፣ መሹለኪያ በሮቹ ተከፈቱ፣ እና የእኔ አጎት፣ ከሌሎች ጋር በአንድ ላይ የእሳተ ገሞራ ቅልጥ ድንጋይ ውስጥ ወደታች ወደቀ። እነሱ ሁሉም ጮኹ።

በዛ የስቃይ ግዛት ውስጥ ካሉ (ከነበሩት) ሰዎች መሐከል - **እግዚአብሔር**ን የማያውቁ የነበሩት - ብዙዎቹ የቡድሂስት መነኮሳት ናቸው፣ አንዳንዶቹ ወደ ዓለም በኃጢአት የተመለሱ (ባክስላይድን) ክርስቲያኖች ነበሩ፣ ሌሎች አንዳንዶች ቤተ ክርስቲያን ከ**ኢየሱስ** ውጪ ለሌላ ምክንያቶች የታደሙ (ይታደሙ የነበሩ) ነበሩ።

በሌላ የሲኦል ቦታ፣ **ኢየሱስ** ለእኔ እንዲህ አለኝ:- *"ሀክ-ሱንግ፣ በቅርበት ተመልከት።"* በትልልቅና በትንንሽ እባቦች የተከበቡ ብዙ ሰዎች እዛ ነበሩ። ሁሉም በአንድ ላይ በቅርበት ተቀላቅለው ነበር። ትልልቆቹ እባቦች በሰዎቹ ጭንቅላት ዙሪያ ተጥመለመሉ(ተጠመጠሙ) ትንንሾቹ እባቦች ደግሞ በሰዎቹ አካሎች ዙሪያ ተጠመጠሙ። ትንንሾቹ እባቦች ያለማቋረጥ ይማቱና ይናከሱ(ይናደፉ) ነበር። ሰዎቹ በህመም በታላቁ ይጮኹ ነበር። እኔ **ጌታ**ን ጠየቅሁት፣ *"**ጌታ** ሆይ፣ እነዚህ ሰዎች ምን አይነት ኃጢአት ነው የፈፀሙት?"* **ኢየሱስ** መለሰ:- *"እነሱ እውነተኛ እምነት በእኔ በፍፁም ኖሯቸው አያውቅም፣ እነሱ በእውነተኛ ልብ እኔን አምነውኝ በፍፁም አያውቁም። በእኔ እንደሚያምኑ ቢናገሩም እንኳ፣ ሥራቸው ጽኑ አልነበረም። እነሱ ሀሳባቸውን ይለዋውጡ ነበር። ሀሳባቸውን የመለዋወጥ ባህሪያቸው የቤተ ክርስቲያን መገኘታቸው (አቴንዳንስ) ላይ ተጽእኖ አሳድሯል። እነሱ በፍፁም በእውነት ዳግም አልተወለዱም። አብዛኛዎቹ ሁሉም በኢደጋዎች ነው የሞቱት፣ እና እነሱ በሙሉ ንሰሃ መግባት (መጸጸት) አልቻሉም ነበር። ሀክ-ሱንግ፣ አንተም እንኳ ሐሳብን የመለዋወጥ ስብዕና አለህ። ነገር ግን፣ የክርስቲያን አካሄድህ የተደላደለ (ጽኑ) ነው።"*

በሌላ የሲኦል ክፍል ውስጥ፣ አንድ ሴት እጅግ በጣም በከፍተኛው እያለቀሰች አስተዋልኩ፣ *"ይህ ፍትሃዊ አይደለም! ይህን አይነት ቅጣት አይገባኝም፣ በመሬት የነበረው ሕይወቴ የተመሰቃቀለ ነበር። ከዚህ በላይ ልሸከመው አልቻልኩም። ለዛ ነው ራስን ማጥፋት የፈፀምኩት። ነገር ግን፣ በሲኦል ያለው ህመም በመሬት ላይ ካለው አኗኗር በላይ የማይቻል ነው። ለምንድን ነው ወደ ሲኦል የላከኝ? ይህ አግባብ(ፍትሃዊ) አይደለም። ስለ ሲኦል እውነታዎች በፍፁም ሰምቼ አላውቅም። ለእኔ እዚህ መሆኔ አግባብ(ፍትሃዊ) አይደለም።"* እሷ ይህን ደግማ ደጋግማ ተናገረችው። ከክፉ መናፍስት አንዱ ሳቀና እንዲህ ብሎ መለሰ፣ *"እኔ ራስሽን ወደማጥፋት ውስጥ እንድትገቢ በሙሉ(ፈጽሞ) አስቼሻለሁ። አንቺ እውነቱን አላወቅሽም። ቤተ ክርስቲያን እንኳ ተካፍለሽ ነበር ግን ስለ መንግሥተ ሰማይ ወይም ስለ ሲኦል በፍፁም አልሰማሽም። ስለዚህ ቦታ ትማሪያለሽ(እየተማርሽ እንደሆነ) ብዬ ፈርቼ ነበር። ቤተ ክርስቲያን የተካፈልሽ ቢሆንም፣ አንቺ ራስሽን ገደልሽ። ስለዚህ ለአንቺ እዚህ መሆን አግባብ(ፍትሃዊ) ነው። እኔ ብልጥ ሆንኩብሽና አሳትኩሽ(አታለልኩሽ)። እኔ ነፍስሽን አሸነፍኩ።*

*እኔ ለዘላለም ሁሉ ብዙ ትምህርቶችን አሳይሻለሁ።”* ፍጡሩ ሴቷን ያለምህረት ይመታት ጀመር። ለምህረት ከፍ ያለ ጬኸቷና ልመናዋ ያለ መልስ ይካሄድ ነበር።

**ኢየሱስ** ወደ ቤተ ክርስቲያን መልሶ ወሰደኝ፣ እና በልሳኖች መጸለይ ቀጠልኩኝ። እርሱም ይህን ነገረኝ:- “***ሀክ-ሱንግ፣ ከሌሊት እስከ ንጋት ጠዋት ድረስ የሚቆዩት ጸሎቶችህ በቀን ከሚደረጉት ጸሎቶችህ በላይ እጅግ በጣም ብቁ ችሎታ ያላቸውና ሀይለኛ ናቸው። ስለዚህ፣ ቀን ከመጸለይ በላይ በሌሊት ብዙ ለመጸለይ ሞክር።”***



ወደ እርሱ(እርሱን) የበለጠ በቅርበት እንድመለከት ነገረኝ፣ **ጌታ**ን የእሾሆች ዘውድ ጭንቅላቱ ላይ ጭኖ አየሁ፣ እና እጆቹና እግሮቹ ላይ ያሉትን ቀዳዳዎች አየሁ። ከእያንዳንዱ ቀዳዳ ደም እየፈሰሰ ነበር። የ**ጌታ**ን ሥቃይ እየተመለከትኩ እያለ ንስሐ መግባትና ማልቀስ ቀጠልኩ።

መጸለይ ከጨረስኩ በኋላ፣ **ጌታ** ወደ መንግሥተ ሰማይ ወሰደኝና እንባዎቼን አበሰ። እንደ ንጹህ መስታወት የሆነውን የመንግሥተ ሰማይን ውቅያኖስ አየሁ።

**<u>ሊ, ዩ-ክዩንግ:</u>**

አብዛኛውን ጊዜ ጸሎቶቼን ስጀምር ክፉ መናፍስት እየነዘነዙ ያሰቃዩኛል። ዛሬ ግን፣ **ጌታ** አገኘኝ። እርሱ መታየት ብቻ አይደለም ያደረገው፣ ግን ወደ ገነት ወሰደኝ። **ኢየሱስ** እንዲህ አለ:- “***ዛሬ ጥሩ ተሰምቶሻል፣ አይደለም እንዴ?***” እኔም መለስኩ፣ *“አዎ፣ **ጌታ** ጥሩ ይሰማኛል ምክንያቱም ክፉ መናፍስትን ዛሬ አላየሁም።”*

በመንግሥተ ሰማይ፣ **ጌታ** ወደ አንድ እጅግ ከፍታ ቦታ ወሰደኝና መሬትን አሳየኝ። ከእንደዚህ አንድ ከፍተኛ ርቀት መሬት እጅግ ትንሽ ሆና ታየች። መሬት እየተሸከረከረች እንደሆነ ተገነዘብኩ። **ጌታ**ን ጠየኩት፣ *“**ኢየሱስ**፣ እኔ በመንግሥተ ሰማይ መኖር እፈልጋለሁ። ወደ መሬት መመለስ አልፈልግም።”* **ኢየሱስ** መለሰ:- “***የአንቺ ጊዜ አሁን አይደለም። መጀመሪያ እኔን ማገልገልና በቀናኢነት የእኔን ሥራ መስራት አለብሽ። በተመረጠ ሰዓት አንቺ እዚህ ትመጪያለሽ።”***

**ጌታ** እና እኔ በመንግሥተ ሰማያት ምርጥ ጊዜ አሳለፍን። ቀልዶችን አደረግንና በጣም ሳቅን። ጥሩ ጊዜ ነበረን፣ እና እጅግ በጣም ተደሰትኩ። ከቆይታ በኋላ **ጌታ**ና እኔ ወደ ቤተ ክርስቲያን ተመለስን።

**<u>እህት ቤይክ, ቦንግ-ንዮ:</u>**

ጸለይኩ፣ *“**ጌታ** ሆይ በገንዘብ በኩል(ፋይናንሺያሊ) ልትባርከን ቃል የገባሽውን ለምንድን ነው ያልጠበቅሽው? ቃል የገባሽውን ሰብረሻል። እኛን ተመልከተን። እኛ ስንጸልይ፣ በቅዝቃዜ ውስጥ ነው የምንጸልየው ምክንያቱም ማሞቂያ(ሙቀት) መግዛት ስለማንችል። እየጸለይን እያለ፣ እንንቀጠቀጣለን፣ እና ሞቃት ሆኖ ለመቆየት በተደጋጋሚ እጆቻችንን በአንድ ላይ ማሻሸት አለብን። አንተ ለምን እንዳልባለከን አልገባኝም። ከእሩዝና ከኪምቺ* (ቅመም የበዛበት ከጥቅል ጎመን የሚሰራ፤ የኮሪያ ብሄራዊ ምግብ) *በስተቀር የምንበላው ምንም የለንም... የፓስተሩ ቤተሰቦች ገንዘብ የላቸውም እና የእኔም ቤተሰቦች ገንዘብ የላቸውም። እኛ እየታገልን ነው... ሌሊቱን ሙሉ ስንጸልይ፣ በዛ አኳኋን ከመቀመጣችን የተነሳ እኛ ደርቀንና አብጠናል። አካላቶቻችን በሥቃይና በድርቀት ታሟል። ከተሟላ ምግብ እጥረት የተነሳ ጠንካራ አካላቶች የሉንም። እንደዛ እንድንቀጥል ለምንድን ነው የፈቀድከው? **ጌታ** ሆይ፣ ከዚህ በላይ ልሸከመው አልችልም።”* በመጀመሪያ ሳላስብ እያጉረመረምኩና ቅሬታ እያቀረብኩ ነበር። **ጌታ** ግን በቅንነት እያንዳንዷን ቃል እያዳመጠና እየሰማ ነበር። **ጌታ** በእውነት ከእኔ ጋር ታግሶ ነበረ። በሞቃት ቃላት፣ ጌታ በእርጋታ መናገር ጀመረ:- “***ቅሬታዎችሽ አያስቸግሩኝም። ስለ ምንም ነገር መጨነቅ አያስፈልገንም።”***

ከዛ ሲኦልን ሊያሳየኝ ጀመረ። “***እንሂድ። አሁን፣ ይህን ሁኔታ ተመልከቺ፣***” አለ **ኢየሱስ**። ከዛ እንደ አንድ ተራራ ትልቅ የሆነ አንድ አውሬ አየሁ። አርጃኖ (አዞ) ወይም ድራጎን ይመስላል፣ እና እናቴ ከአውሬው ቀጥላ ነበረች። ተጎጂዎቹን ለመጠቅለል ምላሱን ይጠቀም ነበር፣ እና ከዛ እያንዳንዱን ሰው ያኝክና ይውጣል። እኔ አነባሁ እና አነባሁ። “***ቦንግ-ንዮ፣ ስታለቅሺ፣ ሥቃይሽ ይሰማኛል። ልብሽ ሲያዝን፣ የእኔም ልብ ያዝናል። አንቺ ስታዝኚ፣ እኔም አዝናለሁ። እናትሽ አሁን በህይወት ያለች ቢሆን ኖሮ፣ በረዳሁሽ ነበር። ነገር ግን፣ በጣም ዘግይቷል። ቅሬታ ማቅረብና መናደድ ከፈለግሽ፣ እንደዛ ልታደርጊ ትችያለሽ። እኔ ልብሽን ለማዳመጥ እዚህ እሆናለሁ። እንደተጨነቅሽ(እንደተጎዳሽ) አውቃለሁ። ሁሉንም ወደ ውጭ እንድታወጪው እመኝልሻለሁ።”***



ከቆይታ በኋላ የፓስተራችንን አባት በሲኦል አየሁ። አንድ ክፉ ፍጥረት በውስጡ የበሰበሰ የሚነድ ፈሳሽ እሳት ወዳለበት ወደ አንድ ትልቅ ማሰሮ ወደ ሚመስል ውስጥ ሊወረውረው ዝግጅቱን ጨርሶ ነበር። እኔ **ጌታን** የፓስተሩ አባት ለምን እዚህ እንዳለ ጠየኩት። **ኢየሱስ** መለሰ:- *"እሱ እጅግ በጣም ሀጢአት ሰርቷል እና ለሚስቱ ዘለፋ (ሚስቱን ይሳደብ ይዘልፍ) ነበር። መጠጣት ይወድ ነበር። አልኮል ጧአቱ ነበር። የአልኮል ሱሰኛነቱ የእሱን ሥራ አቃውሶታል፣ እና የራሱን ልጆች ችላ አላቸው። ልጆቹ አስቸጋሪ ህይወት ነበራቸው። በዛም ምክንያት ውጤቱ፣ በዚህ በበሰበሰ የእሳት ፈሳሽ ውስጥ ለዘላለም ይቀምስና ይሰቃያል።"* የፓስተሩ አባት መጮህ ጀመረ:- *"አሀ፣ በጣም ብዙ መጥፎ ነገሮችን አድርጌያለሁ። ሚስቴ **ኢየሱስ ክርስቶስን አዳኟና ጌታዋ** አድርጋ ተቀብላ ቢሆን ብዬ እመኝ ነበር። እሷ ከዛ መንግሥተ ሰማይ መግባት እንድትችል። በምድር ላይ ኢያለሁ ሙሉቀን እቆምርና እጠጣ ነበር። ቤተሰቤን ተንከባክቤ በፍፁም አላውቅም። እኔ የእነሱን መሰረታዊ ፍላጎቶች አላሟላሁም ነበር። ልጆቻችንን ለመመገብ ሚስቴ ቀኑን ሙሉ ትሰራ ነበር። ለእሷ አስቸጋሪ ኣኗኗር እኔ ሀላፊነት አለብኝ። የፈፀምኳቸው ኃጢአቶቹ አሁን ዋጋቸውን እያገኙ ናቸው። መረገም ይገባኛል። እባክሽን፣ ወደ ዓለም ስትመለሽ፣ ቤተ ክርስቲያን መከታተል እንዲቀጥል ትንሹን ልጄን ንገሪው። ለ**ጌታ** ታማኝና አማኝ እንዲሆን ንገሪው።"* ቤተ ክርስቲያን በከንቱ እንዳይከታተሉ ለልጆቹ እንድነግራቸው እሱ በድጋሜ ጠየቀኝ። እነሱ እሁድን ቅዱስ አድርገው መጠበቅ፣ በግልጽ ከልባቸው ንስሐ መግባት፣ እና እንደ ክርስቲያን ከ**ጌታ** ጋር በታማኝነት መራመድ (መጓዝ) አለባቸው።

እሱ ቀጠለ፣ *"እኔ በሲኦል ነኝ እና እየተሠቃየሁ ነው። ሲኦል የመጨረሻ ፍጻሜ እና የማያቋርጥ ሥቃይ ነው። ተስፋ የሌለው ነው። እባክሽን፣ ወደ መንግሥተ ሰማይ ለመሄድ እድል እንዲኖራቸው ለወንድሞችሽ፣ እህቶችሽ እና ለዘመዶችሽ ወንጌልን ስበኪ።"*



**ኢየሱስ** እና እኔ በሲኦል ውስጥ መጓዝ ቀጠልን። እጅግ ብዙ ሰዎች የሲኦልን ሰማይ እንደሞሉ ወደ ተገነዘብኩበት ወደ አንድ ቦታ መጣን። እነሱ ቡዙ የተለያዩ ጎሳዎች ነበሩ፣ እና ሁሉም መስቀሎች ላይ በምስማር ተቸንክረው ነበር። መስቀሎቹ የእንጨት ነበሩ፣ እና እነሱ ልክ ኢየሱስ ተሰቅሎ እንደነበረው ተሰቅለዋል። እኔ ኢየሱስን እነሱ ምን አይነት ኃጢአት እንደፈጸሙ ጠየኩት፣ እና እርሱ በቁጣ የድምጽ ቃና መለሰ፣ *"እነዚህ በመደበኛነት ቤተ ክርስቲያን የሚካፈሉ ሰዎች ናቸው። መጽሐፍ ቅዱሶቻቸውን እንኳ ወደ ቤተ ክርስቲያን ይዘው ይሄዳሉ። ግን እነሱ በከንቱ ያመልኩና ይጸልዩ ነበር። እነሱ አስመሳዮች ነበሩ። እነሱ ግብዞች ነበሩ። ከቤተ ክርስቲያን ውጭ፣ እነሱ ሰካራሞችና አጫሾች ነበሩ። እነሱ ሰንበትን አልጠበቁም። ከቤተክርስቲያን አገልግሎቶች በኋላ፣ የትርፍ ጊዜ እንቅስቃሴዎችን ደግሞ ይወዱ ነበር፣ እንደ ተራራ መውጣትና ሌሎችንም። ከእነዚህ ሰዎች አንዳንዶቹ አራጣ አበዳሪዎች ነበሩ። ገንዘብ ያበድሩና እጅግ ከፍተኛ የወለድ መጠኖችን ያስከፍላሉ። ከፍተኛ የወለድ መጠኖችን እያስከፈሉ ሀብታም እየሆኑ መጡ። ብዙ ቤተሰቦች ከእነሱ የወለድ መጠኖች ጋር መከታተል አልቻሉም ነበር እናም እየከሰሩ መጡ። ከገንዘብ ነክ እጥረት የተነሳ ብዙ ቤተሰቦች ተለያዩ። የእነሱ ልባቸውና ድርጊታቸው ዓለማዊ ነበር፣ ምንም እንኳ ቃላቶቻቸው እምነት ቢያረጋግጥም(ቢጠይቅም)። በሙሉ ልባቸውና ጥንካሬያቸው በእምነት ተራምደው ቢሆን ኖሮ፣ ገነት በገቡ ነበር። ታማኝ ባለመሆናቸው ምክንያት ዳግም መወለድ አልቻሉም። እነሱ ከውሀ ወይ ከመንፈስ ቅዱስ ዳግም አልተወለዱም ነበር። ከእግዚአብሔር ይልቅ ባህልን ተከትለው ነበር። የእነሱ ዓለማዊ እንቅስቃሴዎች የበለጠ ጠቃሚዎች እና ከእግዚአብሔር በላይ ቅድሚያ ይዘው ነበር። ሥራዎቻቸው እውነተኛ እምነትን ኢያሳዩም (ኢይገልፁም)። እነሱ ከልብ ባልሆነ እምነት አገለገሉ።"* ከትንሽ ቆይታ በኋላ ሁሉም ሰዎች በምስማሮች መስቀሎች ላይ ተቸንክረው በትልልቅና በትንንሽ ትሎች ተሸፈኑ፣ ትሎቹም የሰዎቹን ስጋዎች እየሸራረፉ (እየቆረጣጠሙ) ነበር። የሥቃዮች ሥቃይ ነበር። የሀረግ እሾሃማ ግንዶች አንገቶቻቸው ዙሪያ እንዲያደርጉ ተደርገው ነበር። ይህ ሥርአት በተደጋጋሚ ለዘለአለም እንደሚደጋገም **ኢየሱስ** ነገረኝ። **ጌታ** ስለማስጠንቀቂያው እጅግ ጽኑና ግልጽ ነበረ። ከዛ እርሱ (**ጌታ አምላክ ኢየሱስ ክርስቶስ**) በከንቱ ወዳመኑት ሰዎች እንድመለከት ለእኔ ተናገረ።

እኔ ከፍርሀት የተነሳ መግታት በማይቻል መልኩ እየተንቀጠቀጥኩ ነበር፣ **ጌታ** በእርጋታ ለእኔ ተናገረ፣ *"ቦንግ-ንዮ፣ ፈርተሻል። ለዛሬ በቂ ነው፣ እንሂድ። ቦንግ-ንዮ፣ ቤተሰቦችሽ በሥቃይ እንደሆኑ ምስክር ነሽ(አይተሻል)። ይህ ለመቆጣጠር ታላቅ ውል ሆኖዋል። አንቺ እጅግ በጣም አልቅሰሻል። እኔ ላጽናናሽና ላበረታታሽ እመኛለሁ። እኛ መንግሥተ ሰማይ ስንደርስ እና ቤተክርስቲያን ስንገባ፣ እንድትጸልዩ እና አምልኮን እንድታዩ እፈልጋለሁ።"* በመንግሥተ ሰማይ ያለው **የእግዚአብሔር ቤተክርስቲያን** በደማቅ ብርሃን በታላቁ የሚያበራ ነው። የብርሃኑ ፍንጣቂዎች የመንግሥተ ሰማይን ሰማይ ሁሉ ሸፍነውታል። ቤተክርስቲያኑ በእውነት እጅግ በጣም ጥሩ ነበረ፣ ከብዙዎች መላእክትና ቅዱሳን ጋር።

# ==== ቀን 15 ====

**ኪም, ጁ-ኢዩን:**

በኃይል እየጸለይኩ እያለ፣ አንድ ራእይ ከፊቴ ታየ። አንድ ሰው በቤቱ ቲቪ(ቴሌቪዠን) እያየ ነበር። እሱ ቲቪ እያየ እያለ፣ አንድ አስቀያሚ ክፉ መንፈስ ከቲቪው ወጣና የእሱ አካል ውስጥ ገባ። ሰውየው ቲቪ የማየትን መንፈሳዊ ጉዳት በፍፁም አልተገነዘበም። ከዛ ራእዬ ወደ ኢንተርኔት ካፌ ተቀየረ። በሰዎች ተሞልቶ ኢንተርኔት ላይ ከአንድ ሳይት ወደ ሌላ ሳይት ይንቀሳቀሱ ነበር ወይም ጌሞችን በአንድ ቀን 24 ሰዓታት ይጫወቱ ነበር። ቦታው በብዙ ጌም ተጫዋቾች ተሞልቶ ነበር። አንድ ሰው ሙሉ ትኩረቱን ለጌሙ ሰጥቶ ነበር። እሱ ለሰዓታት የተጫወተ መሆን አለበት፣ ዓይኖቹ ቀይ እና በትንሹ በደም






የተመሉ ነበሩ። በድንገት፣ የአጽም ቅርጽ ያለው አንድ ክፉ መንፈስ ከኮምፕዩተሩ ስክሪን ወጣና የሰውየው አካል ውስጥ ገባ። ክፉ መንፈሱ በእሱ ውስጥ እንዳለ፣ እሱ የበለጠ ሱሰኛ እየሆነ መምጣት ጀመረና በጉጉት ተጫወተ። ይህን ካስተዋልኩ በኋላ፣ ኢንተርኔት ላይ ምን እንደምመለከት እና ምን እንደማደርግ የበለጠ መጠንቀቅ እንዳለብኝ ወሰንኩ።

ከዛ በግማሽ ጨረቃ ቅርጽ የሆነ አንድ ክፉ መንፈስ በማስተዋል አየሁኝ። በሚያሸብር አንድ ድምጽ እንዲህ አለ፣ "*ወደ ኢንተርኔት ካፌ እንድሄድ ፍቀድልኝ።*" እና በራእዩ፣ ይህ ክፉ መንፈስ ወደ ኢንተርኔት ካፌ እያመራ አየሁ። ክፉ መንፈሱ ለጌም ሱሰኛ ወደሆነ ወደ አንድ ሰው መጣ፣ እንዲህ አለ፣ "*አንተ በጌሞች በጣም ስለተዋጥክ፣ እኔ አካልህ ውስጥ እገባለሁ።*" ከዛ ያ ክፉ መንፈስ የሰውየው አካል ውስጥ ገባ። ብዙ የሱስ ክፉ መናፍስት በኢንተርኔት ካፌ ውስጥ ያሉትን ሰዎች ይነዘንዙዋቸዋል። አንዳንድ ቅዱሳን እንኳ በዚህ ወጥመድ ውስጥ ይወድቃሉ። እነዚህ ቅዱሳን አጭር ጊዜ በጸሎት ያሳልፉና ብዙ ሰዓታቸውን ከኮምፒዩተሮች ጋር ያሳልፋሉ። እነሱ የቤተ ክርስቲያን ሰዎችን ወደ ኢንተርኔትና ቲቪ ሱስ ውስጥ እንዲወድቁ አድርገዋል። በውጤቱም፣ የእነሱ የቤተክርስቲያን መገኘት እና መንፈሳዊ ሕይወታቸው ተመሰቃቅሎዋል። ክፉ መናፍስቱ ሰዎቹን ለመሳብ ሀላፊ ነበሩ። እኚህ ሰዎች (የኢንተርኔት፣ የቲቪና የጌም ሱሰኞቹ) ታውረው ነበረ እና ክፉ መናፍስት ለሱሰኛነታቸውና ለድርጊታቸው ሀላፊ እንደነበሩ አልተገነዘቡም። በድጋሜ ክፉ መናፍስት ከቴሌቪዠን ወጥተው ወደ ተጎጂዎች አካሎች ውስጥ ሲገቡ ራእይ አየሁ።



ከቆይታ በኋላ በዛ ምሽት፣ መጸለይ ስቀጥል፣ ብዙ ክፉ መናፍስት እኔን ለመዋጋት ጥረታቸውን ቀጠሉ። አንድ መንፈስ በአንበሳ ቅርጽ ከፊቴ ታየ። በጣም አስፈሪ ነበረ፣ እና መንቀጥቀጥ ጀመርኩ። እንዲህም አለ፣ "*እኔ ወደታች ወደ ሲኦል አዳራሾች እወስድሻለሁ።*" እኔ ጮህኩ፣ *"ስለ ምንድን ነው የምታወራው? አንተ የቆሸሸክ ክፉ መንፈስ፣ **በኢየሱስ ክርስቶስ ስም**፣ ሽሽ።"* ከዛ ሸሸ።

ያለምንም እረፍት፣ ሌላ ክፉ መንፈስ ታየ። ለራሴ እንዲህ አልኩ፣ *"ለምንድን ነው ዛሬ ብዙ ክፉ መናፍስት እየታዩ ያሉት?"* በተለየ ሁኔታ፣ ይህ ክፉ መንፈስ በሚያስቅ ሁኔታ ይራመዳል፣ እንደ ዳክዬ። ከመሳቅ በቀር ልረዳ አልቻልኩም። ክፉ መንፈሱ በቁጣ ጮኸ፣ "*ለምንድን ነው እኔ ላይ እየሳቅሽ ያለሽው? አትሳቂ።*" ከጠንካራ ግሳጼ በኋላ ሸሸ።

ከዛ አንድ ክፉ መንፈስ፣ ነጭ ልብስ በለበሰች በአንድ ወጣት ሴት ቅርጽ ታየ። እሷ እንደ ድራኩላ የውሻ ክራንቻ (የእባብ ጥርስ) ነበራት፣ ደም ከአፏ ወደታች እያካፋ ነበረ። እኔን ከመጸለይ ልታምታታኝ(ልታዘናጋኝ) እየሞከረች ነበር። ስለዚህ ለእርዳታ **ኢየሱስ**ን ተጣራሁ፣ እና ፊቷ ላይ መራራ(ክፉ) አስተያየት እየታየባት ሸሸች።

**<u>ሊ, ሀክ-ሱንግ:</u>**

ዛሬ በርከት ያሉ ክፉ መናፍስት አጠቁኝ። የመጀመሪያው አንድ በጣም ትልቅ እንቁራሪት ይመስላል፣ መጥፎ መልክ ነበረው። እኔ እሱን በኢየሱስ ስም ማስወጣት ችዬ ነበረ። ሁለተኛው ክፉ መንፈስ፣ አስቀያሚ የአንድ ሰው ፊት መልክ ነበረው፣ በአንደኛው ጎን በከባዱ በእሳት ተቃጥሏል። **ኢየሱስ**ን ጠራሁ እናም **ጌታ** መጥቶ ታየ። **ኢየሱስ** እየቀረበኝ እያለ፣ ያ ክፉ መንፈስ ሸሸ። ግን **ኢየሱስ** እየደማ እንደነበረ አየሁ(አስተዋልኩ)። እርሱ በዝምታ ቆመና ከፊቴ ሆኖ ደማ። **ጌታ** እያጣው የነበረውን የደም መጠን ላስበው አልቻልኩም። ደሙ ከሁሉም የጭንቅላቱ አቅጣጫዎች እየወጣ ነበር። ማለቂያ የሌለው መስሎ ታየ። ድምጼን ከፍ አድርጌ ከመጠን በላይ አለቀስኩ። **ጌታ** የእጆቹን አንጓዎች ሊያሳየኝ እጆቹን ወደእኔ ዘረጋ። ምስማሮቹ እርሱን በስተው የገቡበትን ቀዳዳዎችና ደሙ ከየት ወጥቶ እየፈሰሰ የነበረበትን አየሁ። **ጌታ** እንዲህ አለ፣ “***ሀክ-ሱንግ፣ ዛሬ ወንጌል መስበክህ ጥሩ ሥራ አድርገሃል። ደግሞ ቤተ ክርስቲያኑን ማጽዳትህ እጅግ ጥሩ ሥራ አድርገሃል።***” በእኔ ጥረቶች እርሱ እጅግ የኮራ ሆኖ ታየና ያመሰግነኝ ቀጠለ፣ “***የእኔ ሀክ-ሱንግ፣ ወንጌል እየሰበክህ እያለ፣ ትንንሾቹን ወንድሞችና እህቶች መራህና ተንከባከብክ። የአየር ሁኔታው እጅግ ቀዝቃዛ ነበረ፣ ግን አንተ እነዛን መሰናክሎች ተወጣሃቸው። አንተ ጥሩ ሥራ አድርገሃል። እኔ በጣም ኮርቼብሃለሁ።***” እርሱ ከዛ አቀፈኝ።

**ኢየሱስ** አንዴ ከሄደ በኋላ፣ አራት መናፍስት ሁሉም በአንድ ጊዜ አጠቁኝ። ከእነሱ መሐከል አንዱ እንዲህ አለ፣ “*አትጸልይ። አቁም። አንተ መጸለይ አትችልም።*” ሌላ ክፉ መንፈስ በፍጥነት ከአንድ ጎን ወደሌላ ጎን ይንቀሳቀሳል፣ ግራ ሊያጋባኝና ሊያዘናጋኝ እየሞከረ። እኔ ትኩረት ላለማጣት በሁሉም ጥንካሬዬ አተኮርኩ፣ እና በልቤ ጮህኩ። በውጤቱም፣ ሁሉም ክፉ መናፍስት ሸሹ።

ከቆይታ በኋላ **ኢየሱስ** ወደ ሲኦል ወሰደኝ። ብዙ ሰዎች እጅግ ትልቅ ከሆነ ከጋለ ጥቁር ማሰሮ ውስጥ ሆነው በሥቃይ ከፍ ባለ ድምጽ እየጮኹና እየጮኹ ያሉበትን አንድ ቦታ እንዳይ ተደረገ። ከማሰሮው ውጪ፣ ቁጥር የሌላቸው (እጅግ ብዙ) ክፉ መናፍስት በሁሉም አቅጣጫዎች እየተራመዱና እየበረሩ ነበረ። **ኢየሱስ** እንዲህ አለ፣ “***ሀክ-ሱንግ፣ አትፍራ፣ እኔ ልጠብቅህ እዚህ እስካለሁ ድረስ ብዙዎቹ ክፉ መናፍስት ሊጎዱህ አይችሉም። ይህ የፈላው ማሰሮ ሥቃይ ቦታ ይባላል። ይህ ለአልኮል ሱሰኞችና የሲጋራ ሱስ ላለባቸው ሰዎች ቦታ ነው።***” ሰዎቹ የፈላው ፈሳሽ ውስጥ ሲገቡ፣ ሥጋቸው ይፈራርሳል። በተለየ ሁኔታ፣ ከፈላው ፈሳሽ ውስጥ እሳት ነበረ። ይህንን ካሳየኝ በኋላ፣ **ኢየሱስ** መልሶ ወደ ቤተ ክርስቲያን ወሰደኝ።

**<u>ሊ,ዩ-ክዩንግ:</u>**

አንድ በአንድ፣ ብዙ ክፉ መናፍስት ሊያምታቱኝ (ሊያዘናጉኝ)ና ሊነዘንዙኝ ሞከሩ። ሁሉንም ገሠጽኳቸው። ከቆይታ በኋላ፣ **ኢየሱስ** አንድ ደማቅ የሚያበራ ልብስ ለብሶ መጣና ታየ። “***ዩ-ክዩንግ፣ ወደ መንግሥተ ሰማይ እንሂድ። መንግሥተ ሰማይ እንደደረስን፣ መላእክት ሰላምታ ሰጡን እና ኢየሱስ በብዙ መጻሕፍት ወደተሞላ ወደ አንድ ክፍል ወሰደኝ።***” እርሱ እየተዘዋወርኩ እንድመረምርና በብዙ የተለያዩ ትምህርቶች ያለውን እጅግ ግዙፉን የመጻሕፍት ስብስብ እንዳነብ ፈለገ። ሁሉም ከወርቅ ተሰርተው ነበረ፣ እና በድንቅ ሁኔታ አምረው በመደርደሪያዎች ላይ ተቀምጠዋል።

***በቁጥር 2 መጽሐፍ ይቀጥላል...***

*የፓስተር ሚካኤል ፓርክ ማረጋገጫ ምስክርነት፣ ኤኤምአይ ተልዕኮ ቤተ ክርስቲያን ዩኤስኤ፣ (714) 537-3397, ኢሜይል: amisbuso ([@]) sbcglobal.net*

*እንደ ፓስተር (እንደ ካህን)፣ ስለ መንፈሳዊ ውጊያ ብዙ መጻሕፍትን እንብቤያለሁ። ይህንን ለመስበክ፣ ለማስተማር እና በሕይወቴ ለመተግበርና በተለያዩ ሀገሮች የተልዕኮ ጉዞ ላይ እጠቀምበታለሁ። ለመጀመሪያ ጊዜ ስለ <u>እጅግ በትልቁ በሀይል እየበራ በሚነደው እሳት መጠመቅ</u> መጽሐፍ ስሰማ፣ በቃ በአንድ በተለየ ርዕስ ከ “እነዛ” መጻሕፍት አንዱ ሊሆን ይችላል ብዬ አሰብኩ። ነገር ግን፣ መጽሐፉን ካነበብኩ በኋላ የመንፈሳዊ ውጊያ የበፊቱ ሀሳቤ ሙሉ በሙሉ ስህተት እንደሆነ እና በመንፈሳዊ ዓይኖቼ ላይ የዓይን ሽፋን እንደነበረኝ*

*ተገነዘብኩ። የፓስተር ኪምን ተከታታይ እጅግ በትልቁ በሀይል እየበራ በሚነደው እሳት መጠመቅ መጽሐፍት ሁሉንም አምስቱንም አንብቤያለሁ። በዓለም ዙሪያ በክርስቲያን የመጽሐፍት መደብሮች ውስጥ የተሸጡ የመንፈሳዊ ውጊያ ብዙ መጻሕፍት አሉ። ብዙዎቹ ፀሐፍያን፣ መጽሐፍ ቅዱሳዊ አስተያየቶችን እያከናወኑ እያለ በራሳቸው ልምዶች ላይ እምነታቸውን ያኖሩ ነበር። ርኩስ መናፍስትንና የክፉትን የጨለማ ሀይላት ለመዋጋት መጽሐፍ ቅዱሳዊ መርህዎችን መጠቀም ተገቢ ነው። ነገር ግን፣ እጅግ በትልቁ በሀይል እየበራ በሚነደው እሳት መጠመቅ ለየት ያለ ነው። ጌታ ኢየሱስ ወደዚህ ትንሽ ቤተ ክርስቲያን መጣና የእያንዳንዱን የቤተክርስቲያኑን አባላት መንፈሳዊ ዓይኖች ከፈተ። የእነሱ መንፈሳዊ ዓይኖች ሲከፈቱ፣ እነሱ ኢየሱስን እና ኢጋንንትን ማየት ይችሉ ነበረ። በእርግጥ ክፉ መናፍስቱን ማየት ችለው(እያዩዋቸው) ሳለ ሰይጣንንና የሰይጣንን ክፉ መናፍስት እንዴት መዋጋትና መቋቋም እንደሚችሉ ጌታ አስተምሯቸዋል። አንዴ መንፈሳዊ ዓይናችሁ ከተከፈተ በኋላ ሰይጣንን መዋጋት እንዴት ቀላል እንደሆነ ማወቅ አስደናቂ ነው። በጣም ብዙ ሰይጣናዊ መናፍስት ህመምን፣ ክፉ አስተሳሰብን፣ የቤተሰብ መሰባበርን፣ የቤተ ክርስቲያን ልዩነቶችን፣ እና በጣም ብዙ ዓይነት ችግሮችን ለማምጣት በዙሪያ አሉ። ማንበቤ በኮሪያ ያለውን የጌታን ቤተ ክርስቲያን (ዘ ሎርድ'ስ ቸርች) እንድጎበኝ ገፋፋኝ፣ ያም በቅርቡ ያደረግሁት ነው። ከፓስተር ኪም, ዮንግ-ዱ እና ከቤተክርስቲያኑ አባላት የእንኳን ደህና መጣህ ሞቃት አቀባበል ተደረገልኝ። በመጽሐፉ ውስጥ ተጽፈው ስላሉት ነገሮች የነበሩኝ ጥርጣሬዎች ፓስተር ኪምን፣ እየጎበኙ የነበሩ ሌሎችንና እዛ የነበሩ ወጣት ሰዎችን በማዋራበት ጊዜ እንደ እንፋሎት ተነኑ። እኔን ያስገረመኝ(ያስደነቀኝ) ቤተ ክርስቲያኑ ከምሽቱ 3:30 ጀምሮ እስከ ጠዋቱ 11 ሰዓት ድረስ( starting at 9:30pm until 5:00 am) በሀይለኛ የጸሎት ወታደሮች ስብስብ ተሞልቷል። በየቀኑ፣ በአንድ ዓመት 365 ቀናት። እነርሱ በምልጃ ጸሎት ተሰማርተዋል። በእያንዳንዱ ሌሊት ሀይለኛ አምልኮ፣ መንፈሳዊ ዳንስ፣ ስብከቶች፣ የቅባት እሳት መስጠት፣ እና ብዙ ጸሎት አለ። በእያንዳንዱ ቀን ጠዋት ፓስተር ኪም በጌታ ኢየሱስ ወደ ሲኦል እንደተወሰደ መስክሬያለሁ። ጌታ ኢየሱስ ሲኦል እውን መሆኗን ፓስተር ኪም ለዓለም እንዲናገር ስለሚፈልግ፣ ጌታ ኢየሱስ የሲኦልን ህመምና ሥቃዩን ፓስተር ኪም እንዲለማመድ(ቱ ኤክስፒሪየንስ ዘ ሰፈሪንግ ኤንድ ቶርመንት ኦፍ ሄል) ይፈልጋል። እሱ (ፓስተር ኪም) ብዙ ጊዜያት ደግሞ ወደ መንግሥተ ሰማይ ተወስዷል። የአሁን ቤተክርስቲያኖች በሲኦል ስለማያምኑ ወይም በምርጡ፣ በቀላሉ ስለሚይዙት፣ ጌታ ኢየሱስ ክርስቶስ አዝኗል። አስደናቂው መጽሐፍ ለሁሉም ክርስቲያኖች በግድ-መነበብ ያለበት መጽሐፍ ነው። እጅግ በትልቁ በሀይል እየበራ በሚነደው እሳት መጠመቅ መንፈሳዊ ጦርነትን(ውጊያን) እንድታሸንፉ ያበረታታችኋል እንዲሁም የመንግሥተ ሰማይን ግሩም መጠነኛ ቅድመ ልምድ ይሰጣችኋል። ቤተ ክርስቲያኔ የፓስተር ኪምን ተከታታይ መጽሐፍት ወደ እንግሊዝኛ ለመተርጎም አቅዷል(አስቧል)። ይህ በዓለም ያሉ ብዙ ክርስቲያኖችን ይጠቅማል እናም መጽሐፍቱን ወደየራሳቸው ቋንቋዎች እንዲተረጉሙት እድል ይሰጣቸዋል።*

[ለአንድ እግዚአብሔር (ቅዱስ አብ ያህዌ ቅዱስ ወልድ ጌታ ኢየሱስ ክርስቶስ ቅዱስ መንፈስ) ምስጋና ይሁን ይሁን አሜን። ማራናታ! ጌታ ኢየሱስ ክርስቶስ የኔ ፍቅር አለኝታዬ አለቴ እወድሃለሁ አፈቅርሃለሁ አምባዬ አምላኬ እኔ ያንተ ባርያ፣ ልጅህ ነኝ አሜን ጌታ ሆይ ናልኝ! ሕዝብህን አድን ርስትህንም ባርክ አባት ሆይ በኢየሱስ ስም አሜን። ኢየሱስም :- "እኔ መንገድ እውነትና ሕይወት ነኝ በእኔ በቀር ወደ አብ የሚመጣ የለም።" አለ። የጌታ ኢየሱስ ክርስቶስ ወንጌል፣ ዮሐንስ 14:6። ሀሌ ሉያ ክብር ለእግዚአብሔር በሰማያት ይሁን አሜን አሜን። ወንድሞቼና እህቶቼ እባካችሁ፣ የዓለም መድኃኒት፣ የዓለም ብርሃን፣ የሰላም አለቃ፣ የዘላለም አባት፣ ታማኝና እውነተኛ ለሆነው፣ ፍቅርና ደግ አምላክ ለሆነው፣ ቅዱስ ጌታ ኢየሱስ ክርስቶስ አምላካችን በእኛ ፋንታ ሀጢአታችንን ተሸክሞ እራሱን እስከሞት ድረስ አሳልፎ የሰጠው፣ ከሙታንም በራሱ ሥልጣን በአባቱም ሥልጣን በቅዱስ መንፈሱም ሥልጣን ለተነሣው፣ ትናንትም አሁንም እስከዘላለም ድረስ በአባቱ በአብ ቀኝ በኃይል ያለው ጌታ ኢየሱስ ክርስቶስን ጌታችሁና አዳኛችሁ አድርጋችሁ ተቀበሉት እመኑበት እርሱ ብቻ ነው የሚያድናችሁ፣ ያለ ኢየሱስ ማንም ዘላለማዊ ሕይወት የለውም፣ ወደ ሲኦል እንዳትወድቁ እርሱን ጌታችሁና መድኃኒታችሁ አድርጋችሁ ተቀብላችሁ በቅድስናና በንጽህና ኑሩ። አንዴ እርሱን የተቀበላችሁም እንደ ጌታ ኢየሱስ አባት ፈቃድ ኑሩ፣ ጌታ ኢየሱስ ክርስቶስን የናዝሬቱን ጌታ ምሰሉት፣ ብርሃናችሁ በሰው ሁሉ ፊት ይብራ። በኃጢአት አትኑሩ፣ እኛ ጌታን የተቀበልን አንዴ ከጌታ ጋር ተሰቅለናል ስለዚህ መጽሐፍ ቅዱስን እያነበባችሁ የጌታ ኢየሱስ ክርስቶስ ፈቃድ ምን እንደሆነ አስተውሉና ሙሉ ልባችሁን ለጌታ ኢየሱስ የሹኣ ሃማሺያክ ስጡት፤ እርሱ ልብንና ኩላሊትን ይመረምራል እግዚአብሔር ፈጣሪ ነውና፣ ስለዚህ ወደኋላ እየተንሸራተታችሁ ያላችሁ በንሰሐ እና በፍቅር ልብ ወደ ጌታ ተመለሱ፣ እርሱ ምህረቱ ታላቅ ፍቅሩም ለዘላለም ነው። ከዚህ ዓለም ስታልፉ፣ ከጌታ ፊት ከመቆማችሁ በፊት በጌታ ኢየሱስ ክርስቶስ ሆናችሁ ንጹህ ሆናችሁ ኑሩ፣ ሳትታክቱ ሁል ጊዜ በጸሎት ከእግዚአብሔር ኢየሱስ ክርስቶስ ጋር ሕብረት አድርጉ፣ ጸልዩ ለዓለም፣ ጸልዩ በጌታ የወይን እርሻ ለሚያገለግሉ ቅዱሳን፣ ጸልዩ ለድሆች፣ ጸልዩ ለእስራኤል ሰላም፣ እንጸልይ ላልዳኑት ድህነት፣ ጸልዩ ለቤተ ክርስቲያን የንጥቀት ዝግጅት፣ ጸልዩ ጌታ ኢየሱስ እንዲያዘጋጃችሁ እንዲያበረታችሁ፣ ጸልዩ የእግዚአብሔር ቃል በሙላት እንዲኖራችሁና እንደፈቃዱ እንድትኖሩ፣ ጸልዩ ስለ ወንጌል ለሁሉም መዳረስና ስለ ሰዎች ከጨለማ እስራት በጌታችን በኢየሱስ ክርስቶስ እውነት ነፃ መውጣት፣ ጸልዩ እስከመጨረሻው በሕያው እምነት እንጸና ዘንድ፣ ጸልዩ ስለ ኢየሱስ ክርስቶስ ፍቅር በልጆቹ ላይ መገለጥና በሙላት መብራት፤ ኢየሱስ በደሙ ያጥባችኋል፣ ጌታ ይወዳችኋል፣ ለጌታ መምጣት ተዘጋጁ በቅድስና ንጽህና፣ እርሱን በመንፈስ ቅዱስ ተሞልታችሁ በመታዘዝና በንጹህ ልብ ጠብቁት፣ እርሱ የቅዱሳን ነብያት አምላክና የፍጥረታት ሁሉ ፈጣሪ ነው ኢየሱስ ክርስቶስ። ከሞታችሁ በኋላ ገነትና ሲኦልን እናንተ አይደለም የምትመርጡት፣ በክርስቶስ ኢየሱስ መኖር አለመኖራችሁና እዚህ ምድር ላይ የጌታ እግዚአብሔር ኢየሱስ ቃልን ማድረግ አለማድረጋችሁ ነው የሚወስነው። ጌታ ኢየሱስን እንደ አዳኝ ባለመቀበላችሁና በቅድስና ባለመኖራችሁ ወደ እሳት ባህር ከመግባታችሁ በፊት አሁን ከጌታ ኢየሱስ የሹኣ ሃማሺያክ ጋር ተታረቁ። የቅዱስ አብን ፈቃድ ሁል ጊዜ ፈጽሙ። መድኃኒት ኢየሱስ በቃሉ ያነጻችኋልና ከእግዚአብሔር ቃል ጋር እለት እለት ሕብረት አድርጉ፤ ሃሌ ሉያ አሜን ክብር ሁሉ ለቅዱስ ጌታ ኢየሱስ ለቅዱስ አባቱና ለቅዱስ መንፈሱም አሜን ክብር ለእግዚአብሔር በሰማያት! ኢየሱስ ክርስቶስ ቅዱስ ጌታ ነው]

በእስራኤል አምላክ በሠራዊት ጌታ፣ በነገሥታት ንጉሥና በጌቶች ጌታ በናዝሬቱ ኢየሱስ ክርስቶስ እርዳታ ከእንግሊዝኛ ወደ አማርኛ የተረጎመው፣ ቶማስ ጌታቸው። Translated to Amharic by Thomas Getachew Tuta, hithomasgetachew@gmail.com